# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ማሻሻያ (መመሪያ ቁጥር 554/2013)

Ethiopia Commodity Exchange Rules Amendment (Directive No. 554/2013)

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን
Ethiopia Commodity Exchange Authority

ሰኔ 15፥ 2009 ዓ.ም

# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ማሻሻያ  ቁጥር 554/2013

## 1. መግቢያ

1.1. የተሻሻለዉን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ቁጥር 553/2013ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

1.2. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ከዚህ በኋላ "የምርት ገበያ" በመባል ይጠቀሳል) በምርት ገበያዉ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 550/1999 አንቀጽ 12(10) መሠረት ይህንን ደንብ ማሻሻያ አዉጥቷል፡፡

1.3. ይህን ደንብ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" ተብሎ ይጠቀሳል) በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 6(3) በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት ካፀደቀዉ በኋላ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

1.4. ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ማሻሻያ ቁጥር 554/2013" በመባል ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

የተሻሻለዉ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ቁጥር 553/2013 (ከዚህ በኋላ ደንብ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል) እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

(1) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ **2.1.10** በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 2.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዑስ አንቀፅ 2.1.10 እስከ 2.1.34 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 2.1.11 እስከ 2.1.35 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"2.1.10 የተከለለ ጥብቅ የማቆያ ስፍራ — ምርት የጫኑ ተሽከርካሪዎች ጫነቱ ተሽከርካሪው ላይ እንዳለ ተሸጦ ገዢው የገዛውን ምርት ለማንሻ በተፈቀደው ጊዜ ወስጥ እስከረከብ ወይም ምርቱ ማጋዘን ገብቶ እስከሚቃመጥ ጊዜ ድረስ የሚቆይበት ደህንነቱ የተጠበቀ ስፍራ ነው፡"

(2) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 2.1.12 ነበረው 2.1.13 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"2.1.13 የክፍያ እና ርክክብ ሚጸሚያ — የግብይቶችን የክፍያና ርክክብ አገልግሎት የሚጥና በምርት ገበያው ስም ለአባላት ለርክክብ ዋስትና የሚሰጥ በክፍያ ተቋምነት ዕውቅና ያገኘ የምርት ገበያው ማሚያ ነው፤"

(3) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ **2.1.36** በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 2.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዑስ አንቀፅ 2.1.35 እስከ 2.1.38 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 2.1.37 እስከ 2.1.40 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

<<2.1.36 የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ የሚደረግ ግብይት - ገዥው የምርቱን፣ የማኪናወን ታርጋ ቁጥር፣ የመጋዘትን ልዩ ሥን-ምህዳር፣ የምርቱን ባለቤት ማንነት አወቆ እንዲገበያይ የሚያስችል ግብይት ነው፡፡"

(4) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ **2.1.41** በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 2.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዑስ አንቀፅ 2.1.39 እስከ 2.1.49 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 2.1.42 እስከ 2.1.52 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

2.1.41 አባል-ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ፡- በባለሥልጣኑ የግብይት ፈጻሚ ት ዕውቅና የተሰጠውና በምርት ገበያው አባል ሳይሆን ወይም የአገናኝ አባል ደንበኛ ሣይሆን ለራሱ ለመገበያየት የተቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች ያሟላ ማንኛውም ሰው ነው፡

(5) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ **2.1.53** በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 2.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዑስ አንቀፅ 2.1.50 እስከ 2.1.60 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 2.1.54 እስከ 2.1.64 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

2.1.53 አነስተኛ የግብርና አምራች፡ - ለንግድ ዓላማ ሣይሆን ለመተዳደሪያው በራሱ ማሣ ላይ የግብርና ምርት የሚያመርት ሰው ነው፡

(6) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 2.1.58 ነበረው 2.1.62 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"2.1.62 የዕቃ ማከማቻ ሠራተኛ በሚኒስቴሩ ወይም በሚኒስቴሩ በተወከለ ሌላ ተቆጣጣሪ አካል ማዘን ወይም የተከለለ ጥብቅ የማቆያ ስፍራን ለማካሄድ የተመዘገበ ምርት ገበያ ወይም ሌላ ሶስተኛ ሰው ነው፤"

(7) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 3.1.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"3.1.2 ቦርዱ አስራ አንድ አባላት ሲኖሩት ሊቀመንበሩን ጨምሮ ስድስቱ አባላት በቀጥታ በሚኒስቴሩ ይሾማሉ፣ የተቀሩት አምስቱ አባላት በምርት ገበያው አባላት ወይም በአባላት ማህበራት በዚህ አንቀጽ ማሰረት ይመረጣሉ።"

(8) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 3.1.7 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"3.1.7 የምርት ገበያው አባላት የሚመርጧቸው እጩ የቦርድ ዳይሬክተሮች በተለያዩ የምርት ዘርፍ በተመጣጠነ ሁኔታ ይሆናል።"

(9) የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ 3.2.1.16 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"3.2.1.16 የምርት ገበያው አስተዳደርን ለማቅላጠፍ የሚያግዙ የተለያዩ ዋና ማምሪያዎችንና ማምሪያዎችን ያቋቁማል እንዲሁም

(10) ከደንቡ ንዑስ አንቀጽ 3.6.1 እስከ 3.6.4 ያሉት እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፡፡

"3.6.1 ቦርዱ የምርት ገበያውን ስራዎች ለማከናወን ልዩ ልዩ ዋና ማምሪያዎችን በማንኛውም ጊዜ ሊያቋቁም ይችላል።

3.6.2 ምርት ገበያው የተለያዩ ዋና ማምሪያዎች ይኖሩታል፡፡ እያንዳንዱ ዋና ማምሪያ በምርት ገበያው የሥራ ኋላፊ ይመራል፡፡

3.6.3 የምርት ገበያው ዋና ማምሪያዎች በሥራ አመራር ማምሪያዎች ይደራጃሉ። የሥራ አመራሩ ማምሪያም ዋና ማምሪያውን ለሚመራው ኃላፊ ተጠሪ በሆነ የመምሪ ሥራ አስኪያጅ ይመራል።

3.6.4 የምርት ገበያው አሜሪር በቦርዱ በሚፀድቅ የምርት ገበያውን ደረጃታዊ መዋቅር እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻል ይችላል።"

(11) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 3.7.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"3.7.1 የምርት ገበያው ከዋና መሥሪያዎች በተጨማሪ ቦርዱ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚወስነውን ያህል የድጋፍ ሰጪ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል፡፡"

(12) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 3.8.3.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"3.8.3.2 ለተፈቀደለት የምርት ገበያው ዋና መሥሪያ ተግባር ወይም"

(13) የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4.1.4 እና 4.1.5 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.1 ስር ተጨምረዋል፡፡ከንዑስ አንቀፅ 4.1.4 እስከ 4.1.6 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 4.1.6 እስከ 4.1.8 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"4.1.4 በተለየ ሁኔታ በሌላ ህግ ካልተደነገገ በስተቀር ለራሱ ወይም ለደንበኛው የሚገበያይ አገናኝ አባል ምርት ገበያው ላይ በሚከሄዱ ግብይቶች መገበያየት የሚችለው በገዢ ወይም በሻጭ ወገን ብቻ በመሆን ነው፡፡

4.1.5 በተለየ ሁኔታ በሌላ ህግ ካልተደነገገ በስተቀር ለራሱ ግብይት የሚፈጽም ተገበያይ አባል ምርት ገበያው ላይ በሚከሄዱ ግብይቶች መገበያየት የሚችለው በገዢ ወይም በሻጭ ወገን ብቻ በመሆን ነው፡፡"

(14). የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 4.3.2.2 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.3.2 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዑስ አንቀፅ 4.3.2.2 እስከ 4.3.2.8 የነበረው ከንዑስ አንቀፅ 4.3.2.3 እስከ 4.3.2.9 ሆኖ ተሸጋሽገዋል፡፡

"4.3.2.2 የአባልነት መቀመጫዎች በጨረታ ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ሊሸጥ ይችላሉ፡፡"

(15) ንዑስ አንቀጽ 4.6.1.4 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.6.1.4 የምርት ገበያው ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገው ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ማመልከቻው ውድቅ ከተደረገ አመልካቹ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቦርዱ አመልካቹ ለአባልነት ብቁ መሆን አለመሆኑን በአብላጫ ድምጽ ይወስናል፡፡ ቦርዱ በአባልነት ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡"

(16) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.6.2.9 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.6.2.9 የሕብረት ሥራ ማህበር ከሆነ የመተዳደሪያ ደንብ"

(17) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.6.4.1(ለ) ተሰርዟል፡፡

(18) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.6.5.3፣ 4.6.5.4 እና 4.6.5.5 እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፣ እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4.6.5.6 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.6.5 ስር ተጨምሯል፡፡

"4.6.5.3 የአባላት ከአባልነት ማግድ ዓመታዊ የአባልነት ክፍያን አያስቀርም፡ ዓመታዊ የአባልነት ክፍያው በሚጀምሪያው ሩብ አመት መከፈል አለበት፡፡ ምርት ገበያው የመክፈያውን ጊዜ እንዳስፈላጊነቱ ሊቀይር ይችላል፡፡

4.6.5.4 ዓመታዊ የአባልነት ክፍያውን መክፈል በሚገባው ቀን ያልከፈለ አባል፤ መክፈል የሚገባውን የአባልነት ክፍያ 10 በመቶ ክፍያ ላዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር እስከ 30 በመቶ የሚደርስ ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

4.6.5.5 ዓመታዊ የአባልነት ክፍያውን ንኡስ አንቀጽ 4.6.5.4 መሰረት በተማከተው ሶስት ወራት ወስጥ ያልከፈለ አባል፤ ለአንድ ወር ከአባልነት ይታገዳል። የአባልነት ክፍያውን በዚህ አንድ ወር የእገዳ ጊዜ ወስጥ ያልከፈለ አባል ለተጨማሪ ሁለት ወራት ከአባልነት እንደታገደ የሚቆይ ሆኖ በዚህ ጊዜ ወስጥ አባልነቱ በምርት ገበያው ሜጅመንት ወሳኔ ይቋረጣል።

4.6.5.6 ከአነስተኛ የግብርና አምራች በስተቀር የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.6.5.3፣ 4.6.5.4 እና 4.6.5.5 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ አመታዊ የእድሳት ክፍያን በተማከተ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡"

(19) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1 የመጀመርያው አረፍተ ነገር እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

" 4.7.1 ምርት ገበያው የመገበያየት መብትን ወዲያውኑ ሊያግድ የሚችልባቸው ሁኔታዎች

በምርት ገበያው የሚወሰዱ ሌሎች እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ ሲከሰት ምርት ገበያው የአባል የመገበያየት መብቶችን በሚፎቸውም ጊዜ ወዲያውኑ ሊያግድ ይችላል፤"

(20) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.2.1 (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሰ) እና (ሸ) በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1 ስር ተጨምረው ከንዑስ አንቀፅ 4.7.1.6 እስከ 4.1.7.9 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡ ንዑስ አንቀጽ 4.1.7.9 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.7.1.9 አባሉ በፍርድ ቤት ከኢኮኖሚ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ።"

(21) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1.10 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ከደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.7.1.9 እስከ 4.1.7.11 የነበሩት ከንዑስ አንቀጽ 4.7.1.11 እስከ 4.1.7.13. ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"4.7.1.10 አባሉ በሞት ከተለየ፡፡"

(22) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1.11 ነበረው 4.1.1.13 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.7.1.13 አባሉ ወሳኔውን እንዲያውቅ በተደረገ በአስር የስራ ቀናት ወስጥ በደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.7.1.11 ስር የተጣለበትን መቀጮ ካልከፈለ ክፍያው ሙሉ ለሙሉ ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ድረስ እገዳው እንዲቀጥል መደረግ አለበት፤"

(23) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1.14 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1 ስር ተጨምሯል፡፡

"4.7.1.14 በንዑስ አንቀፅ 4.7.1 መሰረት የአባል የመገበያየት መብቶች ሲታገዱ የምርት ገበያው ሜጅመንት ለቦርዱ እና ለባለስልጣኑ ስለእርምጃው በተቻለ ፍጥነት ማሳወቅ አለበት፡፡

(24) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.7.2 ርእስ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.7.2 ቦርዱ እንደአስፈላጊነቱ የማበያየት መብትን ለማገድ የሚችልባቸው ሁኔታዎች"

(25) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.2.1 (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሰ) እና (ሸ) በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1 ስር ተጨምረዋል፡፡ የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.2.1 (ሐ) እና (መ) የነበሩት የደንቡ ንዑስ አንቀጾች ንዑስ አንቀፅ 4.7.2.1 (ሀ) እና (ለ) በሚል የተሸጋሸጉ ሲሆን ንዑስ አንቀፅ 4.1.7.1 (ሥ) እና (ረ) ንዑስ አንቀፅ 4.1.7.1 (ሐ) እና (መ) በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

(26) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1.6፣ 4.7.1.7 እና 4.7.1.8 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.2 ስር የተጨመሩ ሲሆን ንዑስ አንቀፅ 4.7.2.1 (ሥ)፣ (ረ) እና ( ሰ) በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

(27) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.7.2.4 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.7.2.4 አባሉ በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.2 መሰረት የታገደ እንደሆነ፣ እገዳው ተፈጻሚ የሚሆነው የምርት ገበያው የእገዳውን ውሳኔ ለአባሉ ካስታወቀ ከ 24 ሰዓት በኋላ ነው።"

(28) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.7.4.3 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.7.4.3 የአባል የማበያየት መብት በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.7.1.6 መሠረት የታገደ እንደሆነ፣ አነስተኛው የተጣራ ንብረት ማጠንን የሚገልጽ መግለጫ ለምርት ገበያው እንደደረሰ እገዳው ይነሳል።"

(29) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.7.4.4 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.7.4.4 የአባል የማበያየት መብት በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.7.1.8 መሠረት የታገደ እንደሆነ፣ አባሉ ግዴታውን ያሟላ መሆኑን በማሳየት ቦርዱን ሲያሳምን እገዳው ይነሳል።"

(30) የሚከተለው አዲስ አረፍተ ነገር በደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.8 ወስጥ ተጨምሯል፡፡

"4.8 የአባልነት መቀመጫ ሚተላለፍ የሚችለው ከዚህ በታች በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው"

(31) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 4.8.2 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.8 ስር ተጨምሯል፡፡ ከደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.8.2 እስከ 4.8.6 ያሉት ከንዑስ አንቀፅ 4.8.3 እስከ 4.8.7 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"4.8.2 በቤተሰብ የሚደረግ ማስተላለፍ

4.8.2.1 በኢትዮጵያ የወርስ ህግ መሰረት የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎች እንዲሁም የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የሟች የአባልነት መቀመጫ ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት ለወራሾቹ ይተላለፋል፡

I. ወራሽ ስለመሆኑ የፍርድ ቤት የወራሽነት ማረጋገጫ ላቀረበ ወራሽ

II. ወራሾች ከአንድ በላይ በሚሆኑበት ጊዜ፡

(ሀ) ወራሾች በአንድነት ሆነው ለሚያቋቁሙት ድርጅት ወይም

(ለ) ወራሾች ለሚወክሉት አንድ ወራሽ

4.8.2.2 የአባልነት መብት የተላለፈለት ሰው በሶስት ወር ጊዜ ወስጥ ወይም ምርት ገበያው በሚያስቀምጠው ሌላ ተጨማሪ ጊዜ የአባልነት ማስፈርት ካላሟላ የአባልነት መቀመጫ ማስተላለፉ ተሰርዞ መቀመጫው ወደ ወርስ ሃብትነት ይመለሳል፡፡

4.8.2.3 በቦርዱ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለት አመት ጊዜ ወስጥ ህጋዊ ወራሽ ካልመጣ ምርት ገበያው የሟቹን የአባልነት መቀመጫ በጨረታ የመሸጥ እና የሽያጩ ገንዘቡን በዝግ የባንክ ሂሳብ የማስቀመጥ መብት ይኖረዋል፡፡"

(32) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.8.2 የነበረው ንዑስ አንቀፅ 4.8.3 ሆኖ ተሸጋሽገዋል እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.8.3 የማስተላለፍ ሥርዐት፣ የአባልነት መቀመጫን ለጨረታና ለግዢ ስለማቅረብ"

4.8.3.1 የምርት ገበያው ለእያንዳንዱ ምርት ገበያ የአባልነት መደብ የአባልነት መብታቸውን ለመሸጥ የሚፈልጉ አባላት የሚያቀርቡት የጨረታ የሽያጭ ዋጋዎች እንዲሁም የአባልነት መቀመጫ እንዲተላለፍላቸው የሚፈልጉ ሰዎች የሚያቀርቡት የግዢ ዋጋዎች የሚመዘገብበት መዝገብ ይይዛል።

4.8.3.2 የአባልነት መቀመጫን መሸጥ የሚፈልግ አባል የጨረታ መነሻ ዋጋ በማቅረብ ለምርት ገበያው የአባልነት መቀመጫ የመሸጥ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

4.8.3.3 ምርት ገበያው በደንቡ ላይ የተቀመጡት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በ|ላ የአባልነት መቀመጫው በጨረታ እንዲሸጥ ያደርጋል፡፡

4.8.3.4 ምርት ገበያው መዝገብ ላይ የተመዘገቡትን የጨረታ የሽያጭና የግዢ ዋጋዎች ይፋ ያደርጋል። የምርት ገበያው በመዝገብ ላይ የሚመዘግበው የጨረታ የሽያጭና የግዢ ዋጋዎች ያቀረቡትን አባላት ሳይሆን ዋጋዎቹን ብቻ ነው።

4.8.3.5 ጨረታው ወይም ሽያጩ ተቀባይነት ካገኘ አባልነት የሚያስተላልፈው ሰው ለምርት ገበያው ለግዢ የቀረበወን ከፍተኛ ዋጋ እንደተቀበለ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት ወይም ሻጭና ገዢ የአባልነት መቀመጫ ለማስተላለፍ የተስማሙበትን ስምምነት ቅጂ በሁለቱም ወገኖች የተፈረመና የተላለፈበትን ዋጋ የያዘ ለምርት ገበያው ማቅረብ አለባቸው፡፡

4.8.2.6 ምርት ገበያወም አባልነት የተላለፈበትን ዋጋ ይፋ ያደርጋል።"

(33) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.8.5.3 በንዐስ አንቀጽ 4.8.5 ወስጥ ተጨምሮአል፡፡

"4.8.5.3 አባልነት የሚተላለፍለት ሰው የአባልነት ማስፈርት በሶስት ወር ጊዜ ወስጥ ወይም ምርት ገበያው በሚያስቀምጠው ሌላ ተጨማሪ ጊዜ ማሟላት አለበት፡፡ አባልነት የሚተላለፍለት ሰው በተጠቀሰው ጊዜ ወስጥ የምርት ገበያውን የአባልነት ማስፈርት ሳያሟላ ከቀረ ምርት ገበያው መቀመጫውን በድጋሚ ለጨረታ ያቀርበዋል፡፡ አባልነት የሚተላለፍለት ሰው የአባልነት መቀመጫ ከፍያወን መጀመሪያ በገዛበት ዋጋ ወይም ምርት ገበያው መቀመጫውን በጨረታ የሸጠበት ዋጋ ከሁለቱ አነስተኛ የሆነው ተመላሽ ይደረግለታል፡፡"

(34) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 4.8.8 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.8 ስር ተጨምሯል፡፡

"4.8.8 አባልነት የተላለፈበትን ዋጋ ስለማሳወቅ

ምርት ገበያው ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ወይም ለሚተካው ሌላ አካል አባልነት የተላለፈበትን ዋጋ እና የተላለፈበትን ሁኔታ ማሳወቅ አለበት፡፡"

(35) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.9.1.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.9.1.2 ምክንያት ካልቀረበና ምክንያቱም በምርት ገበያው ተቀባይነት ካላገኘ በስተቀር፣ ማንኛውም አባል አባልነቱ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ወር ጊዜ ዉስጥ በምርት ገበያው ማገበያየት ካልጀመረ የሚሰጠው የሶስት ወራት ማስታወቂያ ጊዜ እንዳበቃ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ከተገበያየ በኋላ በተከታታይ ለስድስት ወራት ያህል ማገበያየት ካቋረጠ የምርት ገበያው አባልነቱን ሊያቋርጥ አለበት፡፡"

(36) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.9.3.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.9.3.2 አንድ አባል አባልነቱ ሲቋረጥ ተቀማጭ ገንዘቡን መጀመሪያ ባስቀመጠበት ዋጋ እንዲሁም የአባልነት መቀመጫ ክፍያውን መጀመሪያ በገዛበት ዋጋ ወይም በወቅቱ የገበያ ዋጋ አነስተኛ የሆነው ተመላሽ ይደረግለታል።"

(37) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4.17 በደንቡ አንቀፅ 4 ስር ተጨምሯል፡፡

**"4. 17 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ**

4.17.1 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ዓይነቶች (መደቦች)

4.17.1.1 የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚከተሉት ሶስት ዓይነት አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ዓይነቶች ይኖሩታል።

ሀ. አነስተኛ የግብርና አምራቾች
ለ. አቅራቢዎች
ሐ. ላኪዎች

4.17.1.2 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የሚገበያየው በራሱ ስም ብቻ ነው።

4.17.1.3 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ በምርት ገበያው በሚካሄዱ ግብይቶች ማገበያየት የሚችለው ገዥ-ብቻ ወይም ሻጭ-ብቻ በመሆን ነው።

4.17.1.4 የምርት ገበያው የተቀላጠፈ የገበያ አሠራርን ታሳቢ በማድረግ ሌሎች አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ መደቦችን ሊፈጥር ይችላል።

**4.17.2 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይነት መብት ለማግኘት ብቁ ስለመሆን**

በዚህ ደንብ በንዑስ አንቀጽ 4.2 ላይ የተቀመጡ ክልከላዎች አባል ባልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**4.17.3 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ለመሆን መሟላት ስለሚገባቸው መመዘኛዎች**

4.17.3.1 አመልካቾች የሚከተሉትን ሰነዶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

ሀ. ግለሰብ ከሆነ ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ፤ መንጃ ፈቃድ ወይም ፓስፖርት፣

ለ. አነስተኛ ገበሬ ከሆነ ምርቱን ከራሱ ማሳ ስለማሰብሰቡ ከሚማከተው የማግስት ማስሪያ ቤት የተሰጠ ማስረጃ፤

ሐ. አቅራቢ ወይም ላኪ ከሆነ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ቅጅ፤

መ. እንደ አስፈላጊነቱ የግብር ማለያ ቁጥር፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርተፊኬት እና የግብር እዳ የሌለበት ስለማሆኑ ማስረጃ፤

ሠ. በቦርድ የሚተዳደር ከሆነ ቦርዱ ወይም ተመሣሣይ አካል በምርት ገበያው ለማበያየት ሥልጣን የሰጠበት ወሳኔ/ፈቃድ፤

ረ. የሽርክና ማህበር ከሆነ የሽርክና ስምምነት ቅጅ፣

ሰ. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወይም የአክሲዮን ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፉንና የመተዳደሪያ ደንቡን ቅጅ፣

ሸ. የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የመተዳደሪያ ሕገ-ደንቡን ቅጅ፣

ቀ. የመንግስት የልማት ድርጅት ከሆነ የማቋቋሚያ ህጉን ቅጅ፣

በ. በምርት ገበያው መድረክ (በኤሌክትሮኒክ እና በግልጽ) ለማበያይት የሚያስችለውን ስልጠና ስለመወሰዱ የተሰጠውን ሰርተፊኬት፤

ተ. በባለሥልጣኑ በግብይት ፈጻሚነት ዕወቅና

4.17.3.2 ማንኛውም ሰው፣ የንግድ ድርጅት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የኅብረት ሥራ ማኀበር ‹ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ በሚል ለማበያየት ብቁ ለሆን የሚችለው የሚከተሉትን ካሟላ ነው፡-

4.17.3.2.1 አቅራቢ ወይም ላኪ ከሆነ ግዙፍነት የሌለዉ ወይም በእጅ የሚዳሰሰትን ንብረት በመቀነስ የሚገኘውን የተጣራ ንብረት ሊያሟላ የሚገባውን አነስተኛውን ማጠን ስለማያዙ የሚያረጋግጥ በባለሥልጣኑ ዕወቅና ባገኘ ኦዲተር የተመረመረ የፋይናንስ መግለጫ ብር 250,000 ካቀረበ፤

4.17.3.2.2 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይነት ሆኖ ለማበያየት የሚጠየቀውን የመግቢያ ክፍያ ከከፈለ፡-

ሀ. ለአቅራቢ ወይም ላኪ ብር 25,000፤

ለ. ለአነስተኛ የግብርና አምራች ብር 1,000

4.17.3.2.3 አቅራቢ ወይም ላኪ ከሆነ ለምርት ገበያው የግዴታ ሚጸሚያ ዋስትና ማቋቋሚያ የሚሆን ብር 50,000 ከወለድ ነፃ የሆነ የዋስትና ተቀማጭ በጥሬ ገንዘብ ከከፈለ፤

4.17.3.2.4 አቅራቢ ወይም ላኪ ከሆነ አመታዊ የእድሳት ክፍያ ብር 5,000 ከከፈለ

## 4.17.4 አባል ያልሆኑ ቀጥታ ተገበያዮች የግብይት ፈቃድ ስለማግኘት

የዚህ ደንብ አንቀጽ 4.6.4 አባል ላልሆኑ ቀጥታ ተገበያዮች በምርት ገበያው የማበያየት መብት ለማግኘትም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### 4.17.5 አባል ሳይሆኑ ቀጥታ የማበያየት መብትን ስለማግኘት

4.17.5.1 የምርት ገበያ አባል ያልሆኑ ቀጥታ ተገበያዮች ፈቃድ በተወሰነ ጊዜያት፣ የወል ቃሎችና ቁጥር በቦርዱ ወሳኔ ለሽያጭ ይቀርባሉ። አዲስ አባል ያልሆኑ የቀጥታ ተገበያይ መደቦች በቦርዱ ይወሰናሉ። ሁሉም ዓይነት አባል ያልሆኑ ቀጥታ ተገበያይ ዘርፎች ከመውጣታቸው በፊት በቦርዱ መጽደቅ ይኖርባቸዋል፡፡

4.17.5.2የምርት ገበያው አባል ሳይሆኑ ቀጥታ የግብይት ፈቃድ ማግኘት ለሚፈልጉ ተጫራቾች ምርት ገበያው በህዝብ ማስታወቂያ የጨረታ ተሳትፎ ጥሪ ማድረግ አለበት፡፡

### 4.17.6 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የማበያየት መብቶች

4.17.6.1 የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አባል ያልሆኑ ቀጥታ ተገበያዮች በምርት ገበያው የማበያያ ቋሚ መብት የሚያጎናጽፍ የግብይት ፈቃድ ይኖራቸዋል።

4.17.6.2. የደንቡ አንቀጽ 4.1.4 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ በምርት ገበያ የመግዛት–ብቻ ወይም የመሸጥ–ብቻ የማበያየት መብት ይኖረዋል።

4.17.6.3 አባል ያልሆኑ ቀጥታ ተገበያዮች በምርት ገበያው የማበያየት መብት ለሶስተኛ ወገኖች ሊተላለፍ አይችልም።

### 4.17.7 አባል ያልሆኑ ቀጥታ ተገበያዮች ግዴታዎች

4.17.7.1 ማንኛውም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ያሉበትን የተጣራ የክፍያ ግዴታዎቹን በቀጥታለምርት ገበያው የሚፈጸምና ለዚህም ሲባል ዕውቅና ባገኘ የክፍያ ሚፈጸሚያ ባንክ የባንክ ሂሳብ የመክፈት እንዲሁም በእርሱ ስም የክፍያ ትዕዛዞች ከምርት ገበያው ወደ ክፍያ ሚፈጸሚያ ባንክ እንዲተላለፍ መፍቀድ ይኖርበታል።

4.17.7.2 ማንኛውም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ በማናቸውም ጊዜ ለዚህ ደንብ ተገዢ መሆኑና የተፈቀደላቸው ተወካዮቹም ለዚህ ደንብ እና ለሌሎች የምርት ገበያው ደንቦች ተገዢ መሆናቸውን ሚረጋገጥ ይኖርበታል።

4.17.7.3 ማንኛውም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የተፈቀደለት ተወካዩ የዚህን ደንብ ማንኛውንም ድንጋጌ የሚተላለፍ ድርጊት ሚፈጸማ እንዳወቀ ወዲያውኑ ለምርት ገበያው ማስታወቅ ይኖርበታል፡፡”

4.17.7.4 ማንኛውም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የምርት ገበያው ኮሚቴ ወይም ሠራተኞች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የመተባበር ግዴታ አለበት።

4.17.7.5 ማንኛውም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ሀሰት ወይም አሳሳች መሆኑን የሚያውቀውን ወይም በምክንያታዊነት ሊያውቅ የሚገባውን ሚዳ ለምርት ገበያው ማስጠት የለበትም።

4.17.7.6 ማንኛውም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ በተመደበለት የምርት ገበያ የማበያያ ሥርዐት በመጠቀም ለሚያስተላልፈው ትዕዛዝ ሁሉ ኃላፊ ነው። በዚህ መሰረት ለተፈጸመው ግብይትም ተዋዋይ ወገን ይሆናል።

4.17.7.7 ማንኛውም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ በምርት ገበያዉ በየጊዜዉ በሚወሰነዉ መጠንና ጊዜ ለፈፀመዉ ለእያንዳንዱ ግብይት የግብይት አገልግሎት ክፍያ ይከፍላል።

4.17.7.8 ማንኛውም ገዢ-ብቻ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ያሉበትን የተጣሩ የክፍያ ግዴታዎች በቀጥታ በምርት ገበያው ሚዲያም ይኖርበታል። ለዚሁ ዓላማ ቀጥታ ተገበያዩ የክፍያ የመገዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ በምርት ገበያ የክፍያ ሚዲያሚ ባንክ ማከፈት እና ምርት ገበያው በተገበያዩ ስም ለታወቀው ክፍያ ሚዲያሚ የተጣራ ኤሌትሮኒክስ ሂሳብ የመገዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ትዕዛዞችን የመላክ ስልጣን እንዲኖረው መፍቀድ አለበት።

4.7.7.9 ሻጭ-ብቻ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ በምርት ገበያ የክፍያ ሚዲያሚ ባንክ ማከፈት ወይም በክፍያ ሚዲያሚ ባንክ ያለውን የባንክ ሂሳብ ለዚሁ ዓላማ ማስየም አለበት።

4.17.7.10 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ላካሄደው የግዢ ግብይት በምርት ገበያ የወጡ የርክክብ ማስታወሻ እና የማንሻ ማስታወሻ የመቀበል እንዲሁም ተከታትሎ የማስፈጸም ሙሉ ኃላፊነት አለበት።

## 4.17.8 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይን የማበያየት መብት ስለማገድ እና ስለማቋረጥ

4.17.8.1 የማበያየት መብትን ወዲያውኑ ለማገድ የሚያስችሉ ሁኔታዎች

ምርት ገበያው ሊወስድ የሚችለው ሌላ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.7.1 በተቀመጠው አግባብ በምርት ገበያው የማበያየት መብቶቹ ሊታገዱ ይችላሉ፡፡

4.17.8.2 እንደአስፈላጊነቱ የማበያየት መብትን በቦርድ ለማገድ የሚያስችሉ ሁኔታዎች

ምርት ገበያው ሊወስድ የሚችለው ሌላ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.7.2 በተቀመጠው አግባብ በምርት ገበያው ያለው የማበያየት መብትና የተገበያይነት አቋም ሊታገዱ ይችላሉ፡፡

4.17.8.3 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የማበያየት መብት መታገድ ውጤቱ

አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የማበያየት መብቶች መታገድ የሚያስከትላቸው ውጤቶች በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.7.3 መሠረት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

4.17.8.4 የማበያየት መብት እገዳን ስለማንሳት

አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የማበያየት መብት እገዳ የሚነሳበት አግባብ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.7.4 በተቀመጠው መሠረት ይሆናል።

## 4.17.9 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይን የማበያየት መብት ስለማቋረጥ

4.17.9.1 አባል ላልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የተሰጠን የማበያየት መብት ስለማቋረጥ

በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1 እና 4.7.2 ስር የተመለከቱትን ድርጊቶች ከፈጸመ፣ ሚዲያም የማገባውን ሳይፈጽም ከቀረ ወይም ድንጋጌውን ተላልፎ ከተገኘ ቦርዱ እንዳስፈላጊነቱ አባል ላልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የተሰጠው የማበያየት መብት እንዲቋረጥ ሊወስን ይችላል፡፡

4.17.9.2 የግዴታ ቀጣይነት

አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የማበያየት መብት መቋረጡ በማናቸውም መንገድ አባል ያልሆነው ቀጥታ ተገበያይ ለምርት ገበያው፣ ለክፍያ ሚዲያሚ ባንክ ከእንቅስቃሴው ወይም ከተገበያይነቱ በመጣ ያለበትን

ግዴታ ወይም ኃላፊነት አይቀንሰውም፡ አባል ያልሆነው ቀጥታ ተገበያይ ግዴታውን ሙሉ ለሙሉ እስካልተወጣ ድረስም ተጠያቂነቱ የጸና ይሆናል።

4.17.9.3 ስለክፍያዎች ተመላሽነት

4.17.9.3.1 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የማበያየት መብት ሲታገድ ወይም ሲቋረጥ ለምርት ገበያው የተከፈለ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የማበያይነት መብት ማስጠበቂያ ክፍያም ሆነ ዓመታዊ የተገበያይነት አቋም ማስደሻ ክፍያ ተመላሽ አይሆኑም።

4.17.9.3.2 አንድ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የማበያየት መብቱ ሲቋረጥ ወይም ሲታገድ በአንቀጽ 4.17.3.3.2 መሰረት ያስቀመጠው የግዴታ መፈጸሚያ ዋስትና ገንዘብ መጀመሪያ ባስቀመጠበት ዋጋ ተመላሽ ይደረግለታል።

4.17.9.4 እገዳን ወይም መቋረጥን ስለማስታወቅ

4.17.9.4.1 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የማበያየት መብቱ ሲታገድ ወይም ሲሰረዝ የምርት ገበያው አባል ላልሆነው ቀጥታ ተገበያይ ማስታወቂያ እንዲደርሰው ያደርጋል፤፡

4.17.9.4.2 የምርት ገበያው እንደሁኔታው ስለማንኛውም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የማበያየት መብት መታገድ ወይም መቋረጥ እና አባል ያልሆነውን ቀጥታ ተገበያይ በተመለከተ በቀጣይነት ስለተወሰዱት እርምጃዎች ለባለሥልጣኑ ያሳውቃል።

4.17.9.4.3 የምርት ገበያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4.17.9.4.1 መሠረት በሚወጣ ማናቸውም ማስታወቂያ አግባብ ያለውን ውሳኔ ለማስጠት ማኅሻ የሆኑትን ምክንያቶች ታትመው እንዲወጡ ሊያደርግ ይችላል።

## 4.17.10 አባል ላልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ምትክ ሆኖ ሥራ ስለሚያከናውን ሰው

4.17.10.1 የተፈቀደለት ተወካይ

4.17.10.1.1 ማንኛውም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ግብይቱን በተመለከተ አንድ ተወካይ ብቻ የመወከል መብት አለው። የተወከለው ሰው ከግብይት ጋር በተያያዘ ለመወከል የሚፈቀድለት አንድ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገያይ ብቻ ነው፡፡

4.17.10.1.2 የተፈቀደለት ተወካይ የግብይት ተወካይ ወይም ሌላ ተወካይ ሆኖ ሊሰየም ይችላል፡፡

4.17.10.1.3 በአንቀጽ 4.17.10.1.1 እና 4.17.10.1.2 መሰረት የተወከለ ተወካይ በአንድ ወቅት ለሌላ የምርት ገበያው አባል ወይም አባል ላልሆነ ቀጥታ ተገበያይ በተወካይነት ሊሰራ አይችልም፡፡

4.17.10.1.4 የምርት ገበያው ስለ ተወካዩ አሿሿም፣ አሠራር እና ውክልናው ስለሚቋረጥበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል።

## 4.17.11 ትብብርና ግንኙነት ስለመመሥረት

አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ከምርት ገበያው ወይም ሌላ አግባብነት ካለው አካል ጋር በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.12 በተደነገገው መሠረት መተባበር ይኖርበታል።

## 4.17.12 የውጭ አስተዳዳሪዎችን ስለማሳወቅ

ማንኛወም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ከዚህ በታች ከተማለከቱት ወስጥ አንዱ ከተፈጸመ ለምርት ገበያው ወዲያወኑ ማሳወቅ ይኖርበታል:-

4.17.12.1 አባል ያልሆነወን ቀጥታ ተገበያይ ንብረት በተማለከተ ንብረት አጣሪ ኮሚሽነር ወይም ባላደራ ሲሾም፤ ወይም

4.17.12.2 የሽርከና ማህበር ከሆነ የአባል ያልሆነው ቀጥታ ተገበያይ ሸሪክ ሲከስር፤ ወይም

4.17.12.3 አባል ያልሆነው ቀጥታ ተገበያይ የተጣራ ንብረቱ ማጠን (ግዙፍነት የሌለዉ ወይም በእጅ የሚዳሰሰው ንብረት ተቀናንሶ የሚገኘው) በማቸወም ጊዜ በምርት ገበያው ከተወሰነው አነስተኛ የንብረት ማጠን ያነሰ እንደሆነ፤ ወዲያወኑ ለምርት ገበያው ማሳወቅ ይኖርበታል።

## 4.17.13 ተፈጻሚ የሚሆኑ ሕጎችን ስለማክበር

እያንዳንዱ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የምርት ገበያውን ደንቦች፣ የምርት ገበያውን አዋጅ፣ የባለሥልጣኑን አዋጅ፣ እንዲሁም አግባብነት ያላቸዉን ሌሎች ሕጎች ማክበር ይኖርበታል።

(38) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.2.3 (ሐ) እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.2.3 (ሐ) ክፍት የግብይት ክፍለ ጊዜ - የተላኩ ትዕዛዞች የሚገመዱበት የግብይት ክፍለ ጊዜ ነው፣ በዚህ ክፍለጊዜ ቅድመ ማከፈቻ የግብይት ክፍለ ጊዜ ላይ የተላኩ ትዕዛዞችን ትእዛዙ ከመፈጸሙ በፊት ማሻሻል እና ማስረዝ ይቻላል፡፡ ልዩ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ብቻ አዲስ ትእዛዝ ማስገባት ይቻላል፡፡"

(39) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 5.3.6 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 5.3 ስር ተጨምሯል፡፡

"5.3.6 የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ ለሚደረግ ግብይት የሚሆይ ቅድሙ-ግብይት መረጃ **የግብይት ክፍለ ጊዜ ከመከፈቱ ቢያንስ ከግማሽ ሰአት በፊት በተማሳሳይ ጊዜ ለሁሉም ለተገበያዮች ይፋ መደረግ አለበት፡**

5.3.6.1 ድምጽን በማስተጋባት የሚደረግ ግብይት ላይ የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ የሚደረግ ግብይትን በተማለከተ ሁሉም ቅድሙ-ግብይት መረጃ በማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም ተገቢ በሆነ ሌላ መንገድ ለተገበያዮች እንዲታይ ይደረጋል፡፡

5.3.6.2 በኤሌክትሮኒክ የመገበያያ መድረክ ላይ የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ የሚደረግ ግብይትን በተማለከተ ሁሉም ቅድሙ-ግብይት መረጃ በገበያ ጥልቀት (ሚርኬት ወች) ለተገበያዮች እንዲታይ ይደረጋል፡፡

5.3.6.3 የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ የሚደረግ ግብይትን በተማለከተ የሚሆይ ቅድሙ-ግብይት መረጃ ቢያንስ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፤

I. የምርት ርክክብ ደረሰኝ/የሚከማቻ መጋዘን ደረሰኝ ቁጥር
II. የምርቱ ባለቤት ማንነት፣
III. የማበጠሪያ/ መፈልፈያ ቤት
IV. ወረዳ
V. የምርቱ ደረጃ
VI. የተቀማጠበት ቦታ (መኪና ላይ ወይም መጋዘን ወስጥ)

VII. የምርት ዘመን
VIII. የምርቱን ጥራት የተመለከተ ሚኒስ የያዘ የምስክር ወረቀት
IX. የምርት ጥራት ወጠት (በጥሬው እና ከተቀላ በኋላ)
X. የምርት ማለያ ምልክት
XI. ማዛን ወይም ጥብቅ የሚቅያ ሥፍራው የሚገኝበት ቦታ፣ እንዲሁም ምርት ገበያው አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመባቸው ሌሎች ሚኒጃዎች፡፡

5.3.6.4 የምርት ገበያው አሰራር አንቀጽ 5.3.6.4 ላይ የተጠቀሱትን በማከተት የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ የሚደረግ ምርት ግብይት ወልን ማስያ ማውጣት አለበት፡፡"

(40) የደንቡ ንዐስ አንቀጽ 5.4.2.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.4.2.1 በቃል የሚከተጋባት የግብይት ክፍለ ጊዜ ከማዘጋቱ በፊት ያለው የአንድ ደቂቃ ጊዜ ለእያንዳንዱ የግብይት ክፍለ ጊዜ እንደማዘጊያ ጊዜ ይቆጠራል። የግብይት አሰራር ተቆጣጣሪ ወይም የተመደበ የገበያው ሰራተኛ የማዘጊያ ጊዜው ሲጀምር የመጀመሪያውን የማዘጊያ ጥሪ እንዲሁም የግብይት ጊዜው ሲያበቃ የሚጨረሻውን የማዘጊያ ጥሪ ማሰማት አለበት።"

(41) የደንቡ ንዐስ አንቀጽ 5.4.6.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.4.6.1 ዕለታዊ የአቋም ወሰን አንድ አባል በአንድ የግብይት ቀን እንዲገዛ ወይም እንዲሸጥ የሚፈቀድለት በእያንዳንዱ ወል ወስጥ የተገለፀ ከፍተኛው መጠን ነው።"

**(42)** የሚከተሉት አዲስ ንዐስ አንቀጾች 5.5.1.3፣ 5.5.1.4፣ 5.5.1.5፣ 5.5.1.6 እና 5.5.1.7 በደንቡ ንዐስ አንቀፅ 5.5.1 ስር ተጨምረዋል፡፡ ከንዐስ አንቀፅ 5.5.1.3 እስከ 5.5.1.6 የነበሩት ከንዐስ አንቀፅ 5.5.1.8 እስከ 5.5.1.11 በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

"5.5.1.3 የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ የሚደረግ ምርት ግብይት በተመለከተ የሽያጩ መጠን ካልተገለፀ አንድ መኪና ላይ የተጫነ መሆኑን ጭነት እንደሆነ የሚቆጠር ሲሆን መጠኑን ያልገለፀዉ የሚደረክ ተወካይ አንድ መኪና ላይ የተጫነ ምርት መጠን መሆኑን ግብይት ሚፈጸም ይገደዳል፡

**5.5.1.4 "የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ ለሚደረግ ምርት ግብይት የመጀመሪያ ዋጋ በሻጭ ይሰጣል፡፡ ይህን ተከትሎ ሻጭ በሰጠው ዋጋ ላይ በመመስረት በዋጋ ገደቡ ወስጥ የመጀመሪያ የግዥ ዋጋ በገዢው መስጠት አለበት፣**

5.5.1.5 የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ የሚደረግ ምርት ግብይትን በሚመለከት ገዢዎች ለአንድ የሚከማቻ ደረሰኝ ግብይት በተመደበ የግብይት ጊዜ ተመሳሳይ የመግዣ ዋጋ መስጠት አይችሉም፡

5.5.1.6 የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ ለሚደረግ ምርት ግብይት የሚቀርብ የሽያጭ እና የግዥ ጥያቄ የሚከማቻ ደረሰኝ ላይ የተገለጸውን መጠን ሙሉ ለሙሉ ለመሸጥ ወይም ለመግዛት ብቻ መሆን አለበት፡፡

5.5.1.7 በምርት ገበያው የግብይት መድረክ ላይ የሚፈጸሙ ግብይቶችን ሚጋገጥ በመድረክ ተወካዮች ከሚደረገው በእጅ መሙታት በተጨሪ ምርት ገበያው አግባብ ነው ብሎ በሚያስቀምጣቸው ተጨሪ ግብይቶችን የሚጋገጫ ዘዴ ወይም ምልክት ለፈጸም ይችላል፡፡”

(43) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 5.5.1.12 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 5.5.1 ስር ተጨምሯል፡፡

“5.5.1.12 የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ገላጭ በሆነ ግብይት አንድ የሚከማቻ ደረሰኝ ግብይት ለማካሄድ ቢያንስ አንድ ደቂቃ የሚቆይ የግብይት ክፍለ ጊዜ መመደብ አለበት፤”

(44) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 5.5.2 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 5.5 ስር ተጨምሯል፡፡ የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 5.5.2 የነበረው 5.5.3 በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

“5.5.2 ንዑስ አንቀፅ 5.5.1ን የሚጥስ ተግባር የፈጸመ ወይም በምርት ገበያው የግብይት መድረክ የሚደረጉ ግብይቶች በአግባቡ እንዳይከናወኑ ሊያደርግ በሚችል ሁኔታ የተንቀሳቀሰ የመድረክ ተወካይ በግብይት አሰራር ተቆጣጣሪ ወይም የተመደበ የገበያው ሰራተኛ ከግብይት መድረክ እንዲወጣ ሊደረግ ይችላል፡፡”

(45) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 5.5.2 የነበረው 5.5.3 በሚል ተሸጋሽጓል፡፡ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 5.5.3.1 (መ) (viii) በንዑስ አንቀፅ 5.5.3 ስር ተጨምሯል፡፡ የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 5.5.3.1 (መ) (viii) የነበረው ንዑስ አንቀፅ 5.5.3.1 (መ) (ix) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

“viii. የሚከማቻ ደረሰኝ ቁጥር እና”

(46) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 5.5.4 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 5.5 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዑስ አንቀፅ 5.5.4 እስከ 5.5.20 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 5.5.5 እስከ 5.5.22 በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

“5.5.4 የኤሌክትሮኒክ ግብይት ተወካይ ወይም የራሱን መሙያ የሚያስገባ ደንበኛ ንዑስ አንቀፅ 5.5.3 ን የሚጥስ ተግባር የፈጸመ ወይም በምርት ገበያው የኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ የሚደረጉ ግብይቶች በአግባቡ እንዳይከናወኑ ሊያደርግ በሚችል ሁኔታ ከተንቀሳቀሰ ከግብይት ስርዓቱ ሎግ አውት በመድረግ እንዲወጣ የማይደድ ሲሆን በግብይት አሰራር ተቆጣጣሪ ወይም የተመደበ የገበያው ሰራተኛ ከኤሌትሮኒክ ግብይት መድረክ እንዲወጣ ሊደረግ ይችላል፡፡”

(47) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.5.3 የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5.5.5 በሚል ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

“5.5.5 ግብይቶች

ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ከተሳታፊዎች ማንነት በስተቀር የተፈጸሙ ግብይቶችን ዝርዝር መረጃ በሙሉ ለተገበያዮች እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ የሚደረግ ምርት ግብይትን በሚመለከት የኤሌክትሮኒክ ግብይት መድረክ እንዲሁም

የበቃል በማስተጋባት የማበያያ መድረክ የተፈጸሙ ግብይቶችን ዝርዝር ሚጃ በሙሉ የተሳታፊዎች ማንነት ጨምሮ ለተገበያዮች እንዲታይ ያደርጋል፡፡ የተከናወኑ ግብይቶች በሙሉ በተከናወኑበት ዕለት በክፍያና ርክክብ መሜያ ሙሪት ክፍያ እንዲፈፀም ለምርት ገበያው የክፍያ ሜፀሚ ተቋም መቅረብ አለባቸው።"

(48) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 5.5.7.3 (ሸ) የነበረው 5.5.9.3 (ሸ) በሚከ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"(ሸ) የትእዛዝ አይነት (ገበያ (የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ ለሚያደረግ ምርት ግብይት፣ ገደብ)።"

(49) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 5.5.8.1 የነበረው 5.5.10.1 በሚከ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.5.10.1 እያንዳንዱ በግብይት መድረኩ ላይ ወል የሚዛ ወይም የሚሸጥ የመድረክ ተወካይ ከግብይቱ ጋር የተያያዘ ሚጃ ለማዝ በአባሉ ወይም በተፈቀደለት ወኪል የተሞላና በንዑስ አንቀጽ **5.5.9.3** ሥር የተዘረዘሩትን ሚጃዎች የያዘ የትዕዛዝ ትኬት ማጠቀም አለበት።"

(50) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.5.12.1 የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5.5.14.1 በሚከ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.5.14.1 በግብይት መድረኩ ላይ ወል የገዛ ወይም የሸጠ እያንዳንዱ የመድረክ ተወካይ የመጀመሪያውን የተሞላና የጊዜ ማህተም የተደረገበት የትዕዛዝ ትኬት ቅጂ በግብይት አሰራር ማዝጋቢው እንዲመዘገብ እና ትኬቱ ከተሞላ ምርት ገበያው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ወስጥ ግብይት እንዲፈፀም ማስተላለፍ አለበት።"

(51) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.5.14 የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5.5.16 በሚከ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.5.16 በግብይት መድረኩ ላይ የተከናወኑና የተመዘገቡ ግብይቶችን ሚረጋገጥ

እያንዳንዱ በግብይት መድረኩ ላይ ሽያጭ ወይም ግዥ የሚያስፈፅም የመድረክ ተወካይ ከምርት ገበያው ቅጥር ግቢ ከመውጣቱ በፊት የአባላት ግብይቶች ለክፍያና ርክክብ አፈፃፀም መተላለፋቸውን የሚረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። የክፍያ ርክክብ ሜፀሚ የእያንዳንዱን ምርት መደብ ግብይት ክፍለ ጊዜ ሲያበቃ ለመድረክ ተወካዮ የማስታረቂያ ሪፖርት ማጠጥ አለበት። የግብይት ተወካይ የሚረጋገጫ ሪፓርት ላይ ሜረም በሪፖርቱ ላይ ለተጠቀሱት ግዴታዎች ለማዛት ስምምነት ለመድረሱ ማስረጃ እንደሆነ ይቆጠራል።"

(52) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.5.15(ሀ) የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5.5.17(ሀ) በሚከ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.5.17

ሀ. ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ስርዓት ለኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ እና የራሱን መሜያ ለሚያስገባ ደንበኛ የማስታረቂያ ሪፓርት ማጠጥ አለበት፡፡ የማስታረቂያ ሪፓርት ይዘት እና መቼ እንደሚሰጥ ምርት ገበያው በየጊዜው ለወስን ይችላል፡፡ የግብይት ተወካይ

የሚረጋገጫ ሪፓርት ላይ ሜሬም በሪፖርቱ ላይ ለተጠቀሰት ግዴታዎች ለማዛት ስምምነት ለሚደረሱ ማስረጃ እንደሆነ ይቆጠራል።"

(53) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.5.18.4 የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5.5.20.4 በሚል ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.5.20.4 የምርት ገበያው የማሻሻያ ወይም የማስተካከያ ጥያቄ ዝርዝርን፣ ጥያቄውን ያቀረበውን የግብይት ተወካይ ስምና ማሻሻያው ወይም ማስተካከያውን ያፀደቀውን የግብይት አሰራር ተቆጣጣሪ ወይም የተመደበ የገበያው ሰራተኛ ጨምሮ ሁሉንም የማሻሻያ ወይም የማስተካከያ ዝርዝር ይይዛል።"

(54) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.5.19.1 የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5.5.21.1 በሚል ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.5.21.1 በጉድለት የሚፈፀም ስህተት

የግብይት ተወካይ በደንበኛው የተሰጠውን መመሪያ ሳይፈፅም ከቀረ ወይም ለምሳሌ የታዘዘውን ያህል ባለመግዛት ወይም ባለመሸጥ ደንበኛውን በማስተናገድ ሂደት ስህተት ከሠራ እና መመሪያው ሊያገኝ ከሚገባው ዋጋ ጋር እኩል በሆነ የገበያ ዋጋ ሊፈፀም ካልቻለ የግብይት ተወካዩ ለደንበኛው እና የግብይት አሰራር ተቆጣጣሪ ወይም የተመደበ የገበያው ሰራተኛ ማሳወቅ አለበት። በመቀጠልም ከሚከተሉት እርምጃዎች አንዱን መውሰድ አለበት፡-"

(55) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.5.19.3 (ሀ) የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5.5.21.3(ሀ) በሚል ተሸጋሽጎ የመጀመሪያው አረፍተ ነገር እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

" ሀ. ግድፈት ያለበት ወይም መግባባት የሌለባቸው ግብይቶች ግብይቱ ከማለቁ በፊት የግብይት ተወካዩ የሚከተሉትን ዝርዝሮች በግልፅና በትክክል የሚያሳይ የግብይት ማስተካከያ ደረሰኝ (ከዚህ በኋላ "ደረሰኝ" ተብሎ የሚጠራ) ማዘጋጀት ወይም እንዲዘጋጅ ማድረግ አለበት፡-"

(56) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.5.19.3(ለ) የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5.5.21.3 (ለ) በሚል ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"ለ. ደረሰኙ እንደተሞላ የመድረክ ተወካዩ የትዕዛዝ ቲኬቱን ከደረሰኙ ጋር በማያያዝ ደረሰኙንና የግብይት መዝገቡን ለግብይት አሰራር ተቆጣጣሪ ወይም የተመደበ የገበያው ሰራተኛ ያስተላልፋል። የግብይት አሰራር ተቆጣጣሪው ወይም የተመደበ የገበያው ሰራተኛም ሰነዶቹ የተሟሉ መሆኑንና ደረሰኙ ሜሬማ ሚምሮ በሚረጋገጥ አንዱን ቅጂ ለምርት ገበያው ማስቀረት አለበት።"

(57) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.5.19.3 (ሐ) (i) የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5.5.21.3 (ሐ) (i) በሚል ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"i. የላይኛውን ቅጂ ለግብይት አሰራር ማዘጋቢው ያቀርባል፤ የግብይት አሰራር ማዘጋቢው ደረሰኙ ላይ የጊዜ ማህተም በማድረግ መቀበሉን ያረጋግጣል።"

(58) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 5.5.23 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 5.5 ስር ተጨምሯል፡፡

"5.5.23 በክልል የግብይት ማእከላት የኢንተርኔት መቆራረጥ

በክልል የግብይት ማእከላት የኢንተርኔት በመቆራረጡ ምክንያት የግብይት ክፍለ ጊዜዎችን የሚዋናጉ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ የምርት ገበያው አሜሪር የገበያወን ጥቅም ከግምት ወስጥ በማስገባት አስፈላጊወን እርምጃ ይወስዳል፡፡"

(59) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.6.2.4 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"**5.6.2.4** ለማከማቻት የሚቻለው አነስተኛ ማጠን በምርት ገበያው ግብይት በሚፈረግባቸው ወሎች በሚወሰነው ማጠን ማሰረት ይሆናል፡፡"

(60) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 6.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"6.2 ማዝገብ ሟያዝ

አባላት በምርት ገበያው የተፈቀዱ በሁሉንም ወሎች ላይ የተደረጉ ግብይቶቻቸወን በማዝገብ ሟያዝ አለባቸው። አባላት በምርት ገበያው ለሚፈፅሟቸው ግብይቶች የራሳቸወን ግብይት እና የደንበኞቻቸወን ግብይቶች ማዝገብ ለየብቻ ሟያዝ አለባቸው። አባላት ለእያንዳንዱ ደንበኛቸው ትዕዛዝ የተቀበሉበትን ጊዜና ቀን፣ የተፈፀሙ ዝርዝር ትዕዛዞችንና የሂሳብ ማዝገቦች የያዘ ማዝገብ ለአስር ዓመት በሟያዝ በምርት ገበያው፣ በቦርዱ ወይም/እና በባለሥልጣኑ በተፈለገ ጊዜ ማቅረብ አለባቸው።"

(61) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 6.3.4 ርእስ እንደሚከተለው ተሻሽሎ በፊተት የነበረው አንቀጽ 6.3.4.1 ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

" 6.3.4 አስቀድሞ የተማቻቸ ሽያጭ ወይም ሜድሎ"

(62) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 6.3.4.2 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 6.3.4 ስር ተጨምሯል፡፡

"**6.3.4.2** እያንዳንዱ ሻጭ እና የግብይት ተወካይ በገዢዎች መካከል ማንኛወም አይነት ከፍትሃዊነትና ርትአዊነት የግብይት ሮሆችን የሚቃረን ሜድሎ ከሜድረግ ተከልክሏል።"

(63) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 6.3.8 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"6.3.8 የተፈፀሙ ግብይቶችን ማነወቅ

ማንኛወም በቃል በማስተጋባት በተከናወነ ግብይት ላይ የተሳተፈ የሜድረክ ተወካይ ግብይቶቹ የተፈፀማቡትን ዋጋ ለግብይት አሰራር ማዘጋቢው ወይም ለግብይት አሰራር ተቆጣጣሪ ወይም ለተሰየመው የምርት ገበያ ሰራተኛ ሳያሳወቅ መቅረት የለበትም።"

(64) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 6.4.6.1.1, 6.4.6.1.2 እና 6.4.6.1.3 እንደሚከተለው ተሻሽሏል

"6.4.6.1.1 በግብይት ሜድረኩ የፀና የተዛሜጅ ግብይት ለሚፈፀም ትዕዛዞቹ በሜጀሜሪያ ደረጃ በአንድ የግብይት ክፍለ ጊዜ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ተመሳሳይ ዋጋ በሜድረኩ ተሰጥቷቸው በጨረታ ወይም ለሽያጭ በይፋና በወድድር ቀርበው ጨረታወም ሆነ ሽያጩ በሌላ የማበያያ ሜድረክ ተወካይ ተቀባይነት ካላገኙ ትዕዛዙ በቀጥታ ተፈፅሞ ወዲያው የተዛሜደው ማጠን ማለፅ አለበት

። ይህ ዓይነት ግብይት የግብይት አሰራር ተቆጣጣሪ ወይም የተሰየመው የምርት ገበያ ሰራተኛ በአካል በተገኘበት መፈፀም አለበት።

6.4.6.1.2 የፀና የተዛማጅ ግብይት የሚፈፅም የማበያያ መድረክ ተወካይ ይህንኑ በአግባቡ በተሞላ የትዕዛዝ ቲኬቱ ላይ በግልፅ ማስፈር አለበት። የትዕዛዝ ቲኬቱ ግብይቱ ሲፈፀም ተሞልቶ ወዲያውኑ ለግብይት አሰራር ተቆጣጣሪ ወይም ለተሰየመው የምርት ገበያ ሰራተኛ ለማጣራት፣ የጊዜ ማህተም ለማድረግና ለአጭር ፊርማ መቅረብ አለበት።

1.4.6.1.3 ትዕዛዞችን የሚቀበለው ወይም የሚፈፅመው የመድረክ ተወካይ ከአገናኝነት ወጪ በግብይቱ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የራሱ ጥቅም ሊኖረው አይችልም። አገኛኝ አባሉ ተዛማጅ ግብይት ለፈጸማቸው ሁለት ደንበኞቹ መሃከል ምንም የጥቅም ግጭት እንደሌለ ሚረጋገጫ ሚፈረም አለበት፡፡”

(65) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 6.6 (ረ) እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

“ረ. አሳሳች መሆን፡- የምርቶችን ዋጋ፣ ጥራት፣ ማጠን እና አይነት ማሳሳት ወይም ለማሳሳት መሞከር፣”

(66) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 7.7 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

“7.7 በምርት ገበያው የተፈቀዱ የወል ግብይቶች በሙሉ በክፍያና ርክብክብ ሚፈፀሚያ መመዝገብ ፣ መጣራት እና ሚጸም ያለባቸው ሲሆን ፣ በዚህ ደንብ/የወስጥ ደንብ የሚገዙ ይሆናል።”

(67) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 7.8 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

“7.8 የምርት ገበያው አባላት በግብይት መድረኩ ላይ ለደንበኞቻቸው ለፈጸሙት ለእያንዳንዱ ግብይት የትዕዛዝ ቲኬቶች ማውጣት አለባቸው። እነዚህ የትዕዛዝ ቲኬቶች በምርት ገበያው በተዘጋጀው ቅፅ መሠረት ብቻ ማዘጋጀት አለባቸው። አባላት በምርት ገበያው የግብይት ስርዓት መሠረት ላልተፈፀሙ ሚኖቻቸውም ግብይት የትእዛዝ ቲኬት ማስጠት የለባቸውም።”

(68) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 7.10 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 7 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዑስ አንቀፅ 7.10 እስከ 7.25 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 7.11 እስከ 7.26 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

“7.10 የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ገላጭ በሆነ የግብይት ሥርዓት የተካተቱ ምርቶችን የሚገዙ ገዥዎች የምርቶቹን ወሎች ዝርዝር ቅድመ-ሚጃዎች በአንቀጽ 5.3.6 ላይ በተጠቀሰው ማሰረት ከግብይት አስቀድሞ የማገኘት መብት አላቸው፡፡”

(69) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 7.11 ነበረው 7.12 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

“7.12 የምርት ገበያው ለግብይት የተፈቀዱ ወሎች ዝቅተኛ የዋጋ ጭማሪ እንቅስቃሴ ማጠን፣ የግብይት ማስኪያና ዋጋ የሚጠራው በዚህ ድንጋጌ ለዚያ ወል በተቀማጠው ድንጋጌና ወሉ ለተደረገበት ምርት በተሰጠው ደረጃ መሠረት መሆን አለበት። የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ገላጭ በሆነ ግብይት በምርት ገበያው የግብይት ደንቦች ማሰረት የግብይት ማስኪያና ዋጋ የሚጠራው ከምርቱ ደረጃ በተጨማሪ በማቀማጡ በሌሎች የግብይት ማስኪያዎች የምርቱ ባለቤት፣ የምርቱ በመጠበት አካባቢ፣ የማጠቢያ/የማበጠሪያ ቤቱ፣ እና የማሰሉት ላይ በመሞርኮዝ ነው፡፡”

(70) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 7.16 ነበረው 7.17 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"7.17 የሁሉም የምርት ግብይት ወሎች ርክክብ በምርት ገበያው መጋዘኖች ወይም የተከለሉ ጥብቅ የማቆያ ስፍራዎች ወይም ምርት ገበያው ባፀደቀወና በሰየመው አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ መጋዘኖች ወይም የተከለሉ ጥብቅ የማቆያ ስፍራዎች ወይም የሚፈፀም መሆን አለባቸው።"

(71) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 7.24.1 የነበረው 7.25.1 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"7.25.1 የስልጠና፣ ምርምርና የግብይት ማስፋፍያ መምሪያ የአንደን ምርት መመዘኛ እና ደረጃ ለማውጣት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ ትንታኔዎችን በጽሁፍ በማዘጋጀት የደረሰበትን መደምደሚያ ለዚሁ ምርት ተብሎ ለተቋቋመው የቴክኒክ አማካሪ ጉባኤ (ከዚህ በኋላ "አማካሪ ጉባኤ" እየተባለ ይጠቀሳል) ማቅረብ አለበት፡፡"

(72) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 7.24.2 (ለ) የነበረው 7.25. 2 (ለ) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል

"7.25.2(ለ) ከኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሚወከል አንድ የቴክኒክ ባለሙያ፣"

(73) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 7.24.2.5 የነበረው 7.25.2.5 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"7.25.2.5 የአማካሪ ጉባኤው የምርት ደረጃ እና ክፍፍልን ቴክኒካዊ ጉዳዮች በተመለከተ ለስልጠና፣ ምርምርና የግብይት ማስፋፍያ መምሪያ በጽሁፍ የወሳኔ ሃሳብ ማቅረብ አለበት፡፡"

(74) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 7.24.3 የነበረው 7.25.3 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"7.25.3 ለስልጠና፣ ምርምርና የግብይት ማስፋፍያ መምሪያ ከአማካሪ ጉባኤው በተሰጠው ቴክኒካዊ የወሳኔ ሃሳብ ላይ የገበያ ትንታኔ በማከናወን የግብይት ወል ረቂቅ ማዘጋጀት አለበት፡፡"

(75) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 7.24.5 (መ) የነበረው 7.25.5(መ) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"መ. ሕጋዊ እውቅና ያላቸው የኢንዱስትሪ ማህበራት ወይም ወካይ ተቋማት ከሌሉ ለስልጠና፣ ምርምርና የግብይት ማስፋፍያ መምሪያ የንግድ ዘርፉን በመተንተን አግባብነት ላለው ተወካይ በምርት ገበያው ዋና ስራ አስፈጻሚ ጥሪ እንዲደረግ ለወሳኔ ማቅረብ አለበት፡፡"

(76) ከደንቡ ንዑስ አንቀፅ 7.24.8 እስከ 7.24.10 የነበረው 7.25.8 እስከ 7.25.10 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽለዋል፡፡

"7.25.8 የስልጠና፣ ምርምርና የግብይት ማስፋፍያ መምሪያ ከሚመለከታቸው የምርት ገበያው ዋና መምሪያዎች ጋር በመመካከር እንዲሁም ከአማካሪ ጉባኤው እና ከኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ ያገኘውን አስተያየት በመጠቀም ወሉን የሚጨረሻ ቅርጽ በማስያዝ ከሕግ አንጻር እንዲፈተሽ ለሕግ ማስከበሪያ ዋና መምሪያ ማቅረብ አለበት፡፡

7.25.9 የሕግ ማስከበሪያ ዋና መምሪያ የሚጨረሻ ቅርጽ የያዘወን ወል ለምርት ገበያው ቦርድ ወሳኔ ማቅረብ አለበት፡፡

7.25.10 የሕግ ማስከበሪያ ዋና ማምሪያ የምርት ገበያወን ቦርድ ይሁንታ ካገኘ በኋላ ወሉን እንዲያጸድቀው ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ማኪ አለበት፡ ፡"

(77) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 7.24.13 የነበረው 7.25.13 ሆኖ ተሽጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡ ፡

"7.25.13 ማንኛወም ፍላጎቱ ያለው የምርት ገበያው አባል የወል ማሻሻያ ሃሳቡን ለምርት ገበያው ማቅረብ ይችላል፡ ፡

7.25.13.1 የምርት ገበያው የምርት የቴክኒክ ባለሞያ የቀረበወን የወል ማሻሻያ ሀሳብ ከመረመረና በምርት ገበያው አመራር ይሁንታ ካገኘ በኋላ የወል ማሻሻያ ሃሳቡን ወድቅ ለማድረግ ወይም በንዑስ አንቀፅ 7.24.5 መሰረት ለኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ ለመሪ ይችላል፤

7.25.13.2 የምርት ገበያው በንኡስ አንቀጽ 7.24.13.1 መሰረት በሰጠው ወሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ወሳኔው በደረሰው በአስር ቀናት ወስጥ ይግባኙን ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ማቅረብ ይችላል፡ ፡

7.25.13.3 ባለሥልጣኑ ከላይ በንኡስ አንቀጽ 7.24.13.2 መሰረት በቀረበለት ይግባኝ የሚሰጠው ወሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡ ፡"

(78) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀዕ 7.25.14 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 7.25 ስር ተጨምሯል፡ ፡

''7.25.14 የኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ በንዑስ አንቀፅ 7.24.5 መሰረት ፍላጎቱ ያለው የምርት ገበያው አባል ወይም በምርት ገበያው ያቀረበለትን እና አግባብነት አለው ብሎ ያመነበትን ማንቸውንም የወል ማሻሻያ ሃሳብ ለምርት ገበያው ለማቅረብ ይችላል፡ ፡

''7.25.14.1 የኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ በሰጠው ወሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ወሳኔው በደረሰበው በአምስት ቀናት ወስጥ ይግባኙን ለምርት ገበያው ማቅረብ ይችላል፡ ፡ የምርት ገበያው ይግባኙ በደረሰው በአምስት ቀናት ወስጥ ወሳኔ መስጠት አለበት፡ ፡

7.25.14.2 የምርት ገበያው በሰጠው ወሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ወሳኔው በደረሰው በሰላሳ ቀናት ወስጥ ይግባኙን ለምርት ገበያ ባለስልጣን ማቅረብ ይችላል፡ ፡

7.25.14.3 ባለስልጣኑ ከላይ በንፁስ አንቀፅ 7.24.14.2 መሰረት በቀረበለት ይግባኝ የሚሰጠው ወሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡ ፡"

(79) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 8.2 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 8 ስር ተጨምሯል፡ ፡ ከንዑስ አንቀፅ 8.2 እስከ 8.14 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 8.3 እስከ 8.15 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡ ፡

"8.2 የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ገላጭ የሆነ አቅርቦት ምርትን የጫኑ ተሽከርካሪዎች የተከለሉ ጥብቅ የማቆያ ስፍራዎች ስለማስቀመጥ

**8.2.1** በተከለሉ ጥብቅ የማቆያ ስፍራዎች እንዲቀመጡ በቀረቡና ደረሰኝ በሚቆረጥላቸው ምርቶች እንዲሁም ከረጢቶችና ማጠቅለያዎች ሁኔታ ላይ የመጀመሪያ ምርመራ ማድረግ፣

**8.2.2** የምርት አቅርቦት የጫኑ ተሽከርካሪዎች ላይ የተጫነው ምርት ናሙና ለመወሰድ በተዘጋጀው ቦታ ላይ መውረድ ይኖርበታል፡ ፡

8.2.3 በምርት ገበያው የናሙና አወሳሰድ ሥርዓት መሠረት ወካይ ናሙና መውሰድ ይኖርበታል፣

8.2.4 ከተሽከርካሪው ላይ የወረደውን ምርት ማሉ ለማሉ የምርት አቅርቦቱን ጫኖ ያመጣው ተሽከርካሪ ላይ ተመልሶ መጫን ይኖርበታል፣

8.2.5 በምርት ገበያው የምርት ደረጃ መመዘኛ መሠረት የደረጃ ትንተና ማካሄድ ፣የደረጃ ሪፖርት ቅፅ መሙላት፣

8.2.6 ምርትን መዝኖ የሚዛን ትኬቱን በትክክል መሙላት፣

**8.2.7** የምርት ናሙና ተወስዶ ደረጃ የወጣላቸው እና ሽያጭ የሚጠበቁ የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ገላጭ የሆነ አቅርቦት ምርትን የጫኑ ተሽከርካሪዎች የተከለሉ ጥብቅ የማቆያ ስፍራዎች ወስጥ በወሉ የተጠቀሰው የመቆያ ጊዜ እስከሚያበቃበት ድረስ መቆየት ይችላሉ፡

**8.2.8** የተለያየ ደረጃ የወጣላቸው ምርቶችን የያዙ ጭነቶች መጋዘን ወስጥ ገብተው ይቀመጣሉ፡፡

**8.2.9** የተከለሉ ጥብቅ የማቆያ ስፍራዎች የተቀመጡ የምርት ጭነቶች በተጠቀሰው የመቆያ ጊዜ ወስጥ ካልተሸጡ በወሉ በተጠቀሰው ማስረት መጋዘን ወስጥ ገብተው ይቀመጣሉ፡፡"

(80) የደንቡ ንዐስ አንቀጽ 8.2.1 ነበረው 8.3.1 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"**8.3.1** ምርቱን በምርት ገበያው ለማሻጥ የፈለገ ማንኛውም አባል ወይም ደንበኛ፤ ወይም የአባሉ ወይም የደንበኛው ተወካይ ወይም ማንኛውም ሰው (ከዚህ በኋላ "አስቀማጭ" ተብሎ ይጠቀሳል።) በምርት ገበያው በተሰየመ ማከማቻ መጋዘን ወስጥ ምርቱን ከግብይቱ ቀን በፊት ባለው የሜጨሻ የግብይት ቀን በምርት ገበያው የስራ ሰዓት ወስጥ ማስቀመጥ አለበት።"

(81) የደንቡ ንዐስ አንቀጽ 8.2.3 ነበረው 8.3.3 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"8.3.3 የምርት ገበያው የማከማቻ መጋዘን በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 8.3.2 ስር ካለበት ግዴታ በተጨማሪ ሚኒስቴሩ ባወጣቸው ደንቦች እና መመሪያዎች ማስረት የአቅርቦት ቡና እና ተረፈ ምርት ቡናን የሚመለከት ሚኛ አግባብነት ላለው የመንግስት አካል ሪፖርት ያቀርባል።"

(82) የደንቡ ንዐስ አንቀጽ 8.3.3.5 ነበረው 8.4.3.5 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"8.**4**.3.5 የደረጃ ዝርዝር መመዘኛን ወይም የምርቱን ማለያዎች መሠረት በማድረግ ምርትን ማስቀመጥ፤"

(83) የደንቡ ንዐስ አንቀጽ 8.3.4.1 (ሐ) ነበረው 8.4.4.1 (ሐ) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"ሐ. ምርቱ በማከማቻ መጋዘን በሚቆይበት ጊዜ ደረጃው ወይም የምርቱ ማለያና ማጡ ሳይጓደል ማጠበቁን የሚያረጋግጡ እርምጃዎች መወሰዳቸውንና ጥንቃቄ መደረጉን ሚረጋገጥ፣"

(84) የደንቡ ንዐስ አንቀጽ 8.5.5 ነበረው 8.6.5 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"8.6.5 በማከማቻ መጋዘን ወይም በተከለለ ጥብቅ የማቆያ ስፍራ የሚቀመጡ ምርቶችን ደረጃ ማስጠት የሚችሉት የተመሠከረላቸው የምርት ደረጃ መዳቢዎች (አወጪዎች) ብቻ ይሆናሉ።"

(85) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 8.5.9 ነበረው 8.6.9 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"8.6.9 የምርት ገበያ የሚሰጠው የደረጃ ሠርተፍኬት፣ ኦሪጅናል፣ ግልባጭ ወይም ሌላ ቅጅ ስለ መሆኑ፣ ምርቱ ስለተቀማጠበት መጋዘን ወይም የተከለለ ጥብቅ የማቆያ ስፍራ ስም እና ስለሚገኝበት ቦታ፣ ስለ ምርቱ ደረጃ፣ ሠርተፍኬቱ ስለተሠጠበት ቀን እና የተመሠከረለት የምርት ደረጃ መዳቢ ፊርማን የመሳሰሉ መረጃዎችን መያዝ አለበት።"

(86) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 8.6.3 ነበረው 8.7.3 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"8.7.3 የላቀ ደህንነትን እና ትክክለኛነትን ለሚረጋገጥ እያንዳንዱ ማከማቻ መጋዘን ወስጥ ደረጃ ለመወሰን አገልግሎት የሚሰጡ መሣሪያዎች አግባብነት ባለው የመንግስት አካል ተመርምረው እና ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦ የምስክር ወረቀት ያገኛሉ።"

(87) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 8.9.1 ነበረው 8.10.1 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"8.10.1 ተፈጻሚነት ባለው ሕግ ካልተከለከለ በስተቀር በምርት ገበያው ሽያጭ ሳይፈጸም በማከማቻ መጋዘን ወይም በተከለለ ጥብቅ የማቆያ ስፍራ የተቀማጠ ምርት ከማከማቻ መጋዘን ሊወጣ ይችላል፡፡"

**(88)** ከንዑስ አንቀፅ 8.11.1 እስከ 8.11.2 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 8.12.1 እስከ 8.12.2 ሆነው ተሸጋሽገው እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፡፡

"8.12.1 በማከማቻ መጋዘን ያሉ ምርቶች የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ገላጭ ከሆነ ምርት በስተቀር የአስቀማጩን ማንነት ግምት ወስጥ ሳያስገቡ የተሰጣቸውን ደረጃና ማከማቻ መጋዘን የገቡበትን ቀን መሠረት በማድረግ ብቻ በማከማቻ መጋዘን ይቀመጣሉ።

8.12.2 ወደ መጋዘን የሚገቡት ምርቶች በምርት ገበያው ግብይት የሚፈጸምባቸው ወሎች ወስጥ በተገለጸው መሰኩ ደረጃቸውን በጠበቁ ኬሻዎች መታሸግ አለባቸው፡፡"

(89) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 8.12.6 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 8.12 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዑስ አንቀፅ 8.11.6 እስከ 8.11.14 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 8.12.7 እስከ 8.12.15 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

<<8.12.6 በደንቡ አንቀጽ 8.11.5 ሥር ከተመለከቱት በተጨማሪ ማንኛውም የተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለበት፡-

8.12.6.1 ወደተከለለው ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ የሚመጡ ተሽከርካሪዎችን መቀበል እንዲሁም የምርት መረከቢያ ደረሰኝ እና የምርት መሸኛ ደረሰኝ ለማሠራት የሚያገለግሉ የመኪና መቀበያ ትኬቶችን መስጠት፤

8.12.6.2 የሚገቡና የሚወጡ ተሽከርካሪዎችን መዝገብ መያዝ፤

8.12.6.3 የሚገቡና የሚወጡ ተሽከርካሪዎችን እና የየጭነቶቹን ክብደት ሒሳብ መዝገብ በየዕለቱ የማስታረቅ ሥራ ማከናወን፤

8.12.6.4 ለእያንዳንዱ ጭነት ልዩ የጭነት መለያ ካርዶችን ማሠጠትና በትክክል ማጠበቃቸውን መቆጣጠር፤ እና

8.12.6.5 በእያንዳንዱ የርክክብ ደረሰኝ ስለመቀመጣቸው የተረጋገጠላቸው ምርቶችን የጫኑ መኪኖች አቀማመጥ እያንዳንዱን ጭነት ለይቶ ለማመልከትና ርክክባቸውን ለመፈጸም በሚያስችል ሁኔታ መከናወኑን ማረጋገጥ፡፡ >>

(90) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 8.11.6 ነበረው 8.12.7 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

<<8.12.7 ምርቱን በመከማቻ መጋዘን ወስጥ የሚከማቹትና ከመጋዘኑ የሚወጣት አሠራር መጀመሪያ የገባ መጀመሪያ ይወጣል /መገመዉ/ የሚለዉን መርህ የተከተለ ይሆናል። የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካቸው የታወቀላቸው ጭነቶች አቀማመጥና አወጣጥ የምርቱን ልዩ ማንነት ባስጠበቀ መልኩ መከናወን አለበት፡፡ >>

(91) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 8.11 ነበረው 8.12 ሆኖ ተሸጋሽጎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 8.12.10 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ  ተጨምሯል፡፡

<<8.12.10 የመከማቻ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ብዛታቸው የተከለለ ጥብቅ የማቆያ ሥፍራው ከተመሠከረለት የማስተናገድ አቅም በላይ የሆኑ የአቅርቦት ምርት የጫኑ መኪኖችን ተቀብሎ ማስተናገድ የለበትም፡፡ ሆኖም የተከለለ ጥብቅ የማቆያ ሥፍራው ከተመሠከረለት የማስተናገድ አቅም የበለጠ ቁጥር ያላቸው መኪኖች በሚያጋጥማበት ማጫቸውም ወቅት ምርት ገበያው በቅድሚያ እንዲያወቀው ተደርጎ ያፀደቀው ሲሆን ከአቅም በላይ የማጡት የጭነት መኪኖች ወይም ናሙና የተሠራላቸው ጭነቶች ወደ ጊዜያዊ የተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡ >>

**(92)** ከንዑስ አንቀፅ 8.11.10 እስከ 8.11.14 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 8.12.11 እስከ 8.12.15 ሆነው ተሸጋሽገው እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፡፡

<<8.12.11 በቀዳዳ ወደ ማከማቻ መጋዘኑ ወይም ወደ ተከለለው ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ የሚገባ የወሃ ፍሳሽ መገታት ይኖርበታል። ጥንቃቄ ሚድረጉ ሳይጓደል የተከማቸው ወይም የተጫነው ዕቃ እርጥበት ካዘለ ዕቃው ከሌሎች ተለይቶ ሊቀመጥ የሚገባው ሲሆን ይህንንም የምርት ገበያው ወዲያወኑ እንዲያወቀው መደረግ አለበት።

8.12.12 አግባብነት ባለው የመንግሥት አካል የተከለከለ ዕቃ በማንኛውም ጊዜ በማከማቻ መጋዘን እና በተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ ማስቀመጥ የተከለከለ ነው።

8.12.13 ማከማቻ መጋዘኑ ወይም የተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራው የተማሰከረለትን ምርቶች ለማስቀመጥ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ ለተከለከሉ ዕቃዎች መገልገያ ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።

8.12.14 እያንዳንዱ ማከማቻ መጋዘን ወይም የተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ የገባወን የእሳት አደጋ መከላከያ እና የቁጥጥር መሣዘኛ ኢንሹራንስ ፖሊሲ እንደዚሁም የምርት ገበያው በፅሑፍ ያስቀመጣቸውን የወሳኔ ሀሳቦች ማክበር ይኖርበታል።

8.12.15 እያንዳንዱ የማከማቻ መጋዘን ወይም የተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ ለፀደቀ የክምችት ቦታ እና ለተቆለፈ  የናሙና ሳጥን  የ24 ሠዓት የደህንነት ጥበቃ አገልግሎት  የማስጠት ግዴታ አለበት ። >>

(93) ከንዑስ አንቀፅ 8.12.1 እስከ 8.12.7 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 8.13.1 እስከ 8.13.7 ሆነው ተሻሽሽገው እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፡፡

‹‹8.13.1 የማከሚያ ማዕዘን ሰራተኛ ተባዮችንና አጥፊ እንስሳትን የማከሚያ ማዕዘኑ ወይም የተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራው ከሚገኝበት አካባቢ ለማራቅ ማናቸውንም አስፈላጊ እርምጃ መወሰድ ያለበት ሲሆን እርምጃው የተከማቹ ምርቶች አለማበከላቸውን ለሚረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ የታቀደ መሆን ይኖርበታል። የማከሚያ ማዕዘኑ አሜሪር የቁጥጥር ዘደውን እንደዚሁም ምርመራ የተከናወነበትን ወይም የተበላሸው የተላከበትን ቀን በሠነድ ላይ ማስፈር አለበት።

8.13.2 በተቻለ መጠን ምግብነት ያላቸው ሽርፍራፊ ነገሮችን የማከሚያ ማዕዘን አገልግሎት ከሚሰጥበት አካባቢ ወይም ከተከለለ ጥብቅ የማቆያ ሥፍራ ሜራቅ/ወጪ ሚድረግ ይገባል።

8.13.3 በማከሚያ ማዕዘኑ ወይም በተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራው አካባቢ ያሉ ሁሉም አትክልቶች ከማዕዘኑ ሙረት ቢያንስ በ3 ሜትር ሜራቅ አለባቸው። የማከሚያ ማዕዘኑ አስተዳደር የቁጥጥር ዘዴንና ቀኑን በማዝገብ ማስፈር አለበት።

8.13.4 የማከሚያ ማዕዘን አስተዳደሩ አእዋፍ ማከሚያ ማዕዘኑ ካለበት አካባቢ እንዳርቁ እና ወደ ማከሚያ ማዕዘኑ ወይም ወደ የተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራው እንዳይገቡ ለመከላከል ማንኛውንም አስፈላጊ እርምጃ መወሰድ ያለበት ሲሆን ይህም ጥልፍልፍ ሽቦን ከማስኮት፣ቬንትሌር እና ከማንኛውም ቀዳዳ በላይ መትከልን ያካትታል።

8.13.5 ሁሉም ዓይነት እንስሳትና አእዋፍ ከማከሚያ ማዕዘኑ ወይም ከተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራው እና አካባቢው መወገድ አለባቸው።

8.13.7 የማከሚያ ማዕዘኑን ወይም የተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራውን ከተባይ ለማጠብቅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የዕፅዋት ጥበቃና ተቆጣጣሪ መምሪያ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የተቀበላቸው ፀረ ተባይ መድሀኒቶች ብቻ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። ዚንክ ፎስፈረስን የያዘ ፀረ-አጥፊ እንስሳት መድሀኒት በማከሚያ ማዕዘን ወይም በተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ ወስጥ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም ።››

(94) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 8.13.1 ነበረው 8.14.1 ሆኖ ተሻጋሽነ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

‹‹8.14.1 ማከሚያ ማዕዘኑ ወይም የተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራው በማንኛውም ጊዜ የእሳት አደጋን ከሚያባብሱ ወይም በማከሚያ ማዕዘኑ የተቀማጡ ምርቶች አያያዝን ከሚያሰናክሉ ገለባ፣ ጥራጊ ወይም የዕቃ ክምችት ነፃ መሆንና ንፅህናውም በበቂ ሁኔታ ማጠብቅ ይኖርበታል››

(95) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 8.14 ነበረው 8.15 ሆኖ ተሻጋሽነ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 8.15.3 ተጨምሯል፡፡

‹‹8.15.3 የማከሚያ ቤቱ በምርት ገበያው የመድሀን ሽፋን እንዲደረግላቸው የተወሰነባቸውን ለሌሎችም የአደጋ ዓይነቶች ዋስትና መግባት አለበት፡፡ ››

(96) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 9.1.2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፤

"9.1.2 የአስቀማጩ ፊርማ በምርት ገበያው ሕግ በጠቅላላው እንደዚሁም በማከሚያ ማዕዘኑ፣ በምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከሚያ፣ በክፍያና ርክብክብ ሜጸሚያ ደንቦች በተለይ ለማዛት ስምምነት ለመድረሱ ማስረጃ እንደሆነ ይቆጠራል።"

(97) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 9.1.4 እና 9.1.5 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

<<9.1.4 ወደ ማከማቻ መጋዘን በከፊል ለሚደረግ እያንዳንዱ ምርት ክምችት ይህንኑ የሚያመለክት የእቃ ርክክብ ቮውቸር ይሰጣል። ለሻጩ ወይም ለወኪሉ የተሟላ የእቃዎች ርክክብ ደረሰኝ የሚሰጠው ሙሉ በሙሉ ምርቱ ሲከማች ብቻ ነው።

9.1.5 በማከማቻ መጋዘኑ የዕቃ ርክክብ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ በኤሌክትሮኒክስ እና በህትመት ሚዲያ ማዘዝና ምርቱ ተቀማጭ በሆነበት ቀን ወደ ምርት ገበያው የመጋዘን ኦፕሬሽን ክፍል መተላለፍ አለበት>>

(98) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 9.3.8 እና 9.3.9 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

<<9.3.8 ከማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ ጊዜ ማብቃት፣ ዘግይቶ ከሚከብ እና በምርት ገበያው የተፈጸመ ሽያጭ ሳይኖር ምርትን ከማከማቻ መጋዘን ከማውጣት እንዲሁም ከማከማቻ አገልግሎት ደረሰኝ ይራዘምልኝ ጥያቄዎች ጋር የተያያዙ ቅጣቶችን ማስተዳደር እና

9.3.9 ዘገባዎችን ማጣጣም።>>

(99) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 9.4.1, 9.4.4 እና 9.4.5 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

<<9.4.1 የማከማቻ መጋዘን የዕቃዎች ርክክብ ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ እንደፀደቀ፤ በአንፃሩ ይህንኑ ሚዛን ተንተርሶ ራሱን በራሱ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ደረሰኝ በሚፈጥር ዘመናዊ አሠራር አማካይነት ወዲያውኑ የማከማቻ መጋዘን የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ እንዲወጣለት ይደረጋል።

9.4.4 በምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ መጋዘን የዳታ ማጠባበቂያ ሥርዓት ውስጥ የተከማቸው ዳታ ምርት ገበያው በብቸኝነት በሚቆጣጠረው የተለየ ስፍራ ተጠብቆ መቆየት ይኖርበታል። የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ ከሥራው ጋር የተያያዙ ዳታዎች ባልተፈቀደላቸው ሠዎች እንዳይደረስባቸው በቂ የጥበቃ ሥርዓት ማዘርጋቱን ሚረጋገጥ ይኖርበታል።

9.4.5 የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ በእያንዳንዱ ዝርዝር ሒሳብ ወይም በማከማቻ ደረሰኙ የተረጋገጠው ምርት ያለበትን ወቅታዊ አቋም ወይም በአስቀማጩ ባለቤትነት ማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ውስጥ ለተደረጉ ለውጦች የግብይት ማለያንና የኦዲት መከታተያ እንዲኖር የሚያስችሉ በቂ እርምጃዎችን መወሰድ ይኖርበታል።>>

(100) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 9.4.8 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

<<9.4.8 የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ የዕቃ ርክክብ ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መሠረት አድርጎ እንዲወጣ ይደረጋል። ምርቱን የጫነው መኪና የሠሌዳ ቁጥር፣ የተሣቢው የሠሌዳ ቁጥር፣ የማጠቢያ ወይም የማበጠሪያ ቤቱ፣ ምርቱ የመጣበት ወረዳ፣ የምርት አስተማማኝነት ማረጋገጫ የጥሬ እና የቅምሻ ውጤቶች፣ እና የመሣሠሉት ተጨማሪ ሚዛኖች የምርት ዱካቸው ተለይቶ ለታወቀላቸው ዕቃዎች የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ለማሥራት ግብዓት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ >>

(101) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 9.5.2.3 ሀ፣ሐ እና መ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

‘’9,5.2.3 ስለሽያጭ እና ክፍያ

ሀ. ተበዳሪው እና ባንኩ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙን ለማሻጥ ከተስማሙ በኋላ የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ ሚያዘው ለሽያጭ መቅረብ እንዳይችል የተደረገበትን ሁኔታ እንዲያነሳ እና ለክፍያና ርክብክብ ሚፈጸሚያ ማምርያ የብድር ሂሳቡን ዝርዝር እንዲሰጥ ባንኩ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ትዕዛዝ ማስተላለፍ አለበት፡፡

ሐ. በመቀጠል ተበዳሪው በሞባይ የተሰጠውን የሚከሞቻ ማዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ በምርት ገበያ ለማሻጥ ይችላል፡፡ የምርት ገበያው ክፍያና ርክብክብ ሚጸሜ ማጥያ ሽያጩ ተከትሎ የምርት ገበያውን ክፍያና አግባብነት ያለውን ግብር ከቀነሰ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ በቀጥታ ወደ ባንኩ የብድር ሂሳብ ገቢ ያደርጋል፡፡ የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻም የባለቤትነት መብት ወደ ገዢው ማስተላለፍ አለበት፡፡

መ. በምርት ገበያው የተሸጠውን በሞባይ ተሰጥቶ የነበረ የሚከሞቻ ማዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ክፍያ የምርት ገበያው ለባንኩ ዉዲያውኑ ለማስተላለፍ እንዲችል ባንኩ የተበዳሪውን ስም፣ የምርት ገበያውን የደንበኛ ማታወቂያና የብድር ሂሳብ ቁጥር ያካተተ የተበዳሪውን የብድር ሂሳብ ዝርዝር ሞባዉ ለሽያጭ መቅረብ እንዳይችል የተደረገበት ሁኔታ እንዲነሳ ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር ለምርት ገበያው የክፍያና ርክብክብ ሚጸሜ ማጥያ ማስጠት አለበት፡፡"

(102) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 9.6.2.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

<<9.6.2.1 አቤቱታ አቅራቢ የጥያቄውን ባህሪ በመግለጽ አቤቱታውን ለምርት ገበያው በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡>>

(103) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 9.7.4 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"9.7.4 ስለመዋጮው ዓይነት እና ሂሳብ

የምርት ገበያው በጥሬ ገንዘብ ወይም በሌላ ዓይነት ወይም ዘዴ ለካሳ ፈንዱ መዋጮ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የምርት ገበያው የሚያደርገው መዋጮ የክፍያና ርክብክብ ሚጸሜ ማጥያ በሚያዘጋጀው የካሳ ፈንድ ሂሳብ ገቢ ተደርጎ በየዓመቱ ኦዲት መደረግ አለበት፡፡"

(104) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 9.8 የመጀመሪያው አረፍተ ነገር እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

<<9.8 ስለ አስቀማጩ ሒሳብ

የአባላት ክፍል ለእያንዳንዱ አስቀማጭ የተለየ ሒሳብ /መዝገብ/ መክፈት እና መያዝ አለበት። >>

(105) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 9.8.2 እና 9.8.3 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"9.8.2 ማዕከላዊ ማከማቻ ከማከማቻ ማዘኑ የቀረቡ ጥያቄዎችን ወይም ከክፍያና ርክብክብ ሚጸሜ የቀረቡ መመሪያዎችን በመቀበል በኋላም ይህንኑ የምርት ገበያው ያወጣውን ደንብ ተከትሎ ለአስቀማጩ በሚጋገጥ ከአስቀማጩ ሒሳብ የወጣ ወይም የገባ የማዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ዝውውርን የሚያሳይ መዝገብ መያዝ ይኖርበታል።

9.8.3 በአስቀማጩ ሒሳብ ገቢ የሚደረግ ገንዘብ ማከማቻ ማዘኑ ወይም ክፍያና ርክብክብ ሚፀሜ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በማንኛውም ሜክ ባቀረበው ጥያቄ ወይም በተሰጠው መመሪያ ሊደገፍ ይገባል።"

(106) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 9.9.1.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

<<9.9.1.1 የዕቃ ርክክብ የኤሌክትሮኒክስ ማስታወሻ፣ የርክክብ ማስታወቂያ፣ እና የማንሻ ማስታወሻ መዛግብት፣ >>

(107) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 9.9.1.3 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

''9.9.1.3 ከሚከሚቻ ማዛኑ እና ክፍያና ርክብክብ ሚዜጸሚ  ወይም ለሚከሚቻ ማዛኑ እና ለክፍያና ርክብክብ ሚዜፀሚ  የተላኩ ወይም የቀረቡ ጥያቄዎች እና ትእዛዞች የሚሚከት ማዛግብት ፤"

(108) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.1 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

''10.1 የምርት ገበያው የክፍያና ርክብክብ ሚዜጸሚ

10.1.1 የምርት ገበያው የክፍያና ርክብክብ ሚዜፀሚ  ተግባራት በዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም በዋናው ሥራ አስፈፃሚ የሚሠራ ይሆናል። የዳይሬክተሮች ቦርድ ተስማሚ ሆኖ ሲያገኘው ለዋናው ሥራ አስፈጻሚ ወይም ለሌላ ማንኛውም ክፍያ ፈፃሚ ባንክ ተጨማሪ ሥልጣን ወይም ሀላፊነት በየጊዜው ሊሰጥ ይችላል።

10.1.2 በምርት ገበያው የተደረጉ ውሎች ተጥርተው ክፍያና ርክክብ በምርት ገበያው የክፍያና ርክብክብ ሚዜፀሚ ለፈጸምባቸው የሚባ ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ በግብይቱ ደንብ ወይም ሕግን ተከትሎ ባለሥልጡ በሚሰጠው መመሪያ ወይም ትዕዛዝ መሠረት ማጠናቀቅ / መሠረዝ / ይኖርባቸዋል።"

(109) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

''10.2 የክፍያና ርክብክብ ሚዜጸሚ ተቋም ዋስትና

10.2.1 በምርት ገበያው በየጊዜው የሚወሰኑ የተወሰኑ ምርቶችን የሚሚከቱ እንደዚሁም በዚህ ደንብ መሠረት በምርት ገበያው ግብይት ክፍያቸው ስለሚዜጸም ውሎች አከፋፈል በተሚከተ የምርት ገበያው የክፍያና ርክብክብ ሚዜጸሚ  በአባላት ላይ ስላለ የተጣራ የገንዘብ ግዴታ እንደዚሁም ስለምርቱ ጥራት እውነተኛነት እና ርክክብ ወይም በምርት ገበያው ላይ ስለተደረገ ግብይት ለአባላቱ ዋስትና እንደሠጠ ይቆጠራል።"

(110) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.3.1 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፤

''10.3.1 ሁሉም ተገበያይ አባላት፣አገናኝ አባላት እና ክፍያ ፈጻሚ ገዢ-ብቻ ወስን ተገበያይ አባላት ክፍያ የሚዜጸም ግዴታ ያለባቸው አባላት ናቸው።የምርት ገበያወን የክፍያና ርክብክብ ሚዜጸሚ  የክፍያ አፈጸጸም፣ የርክክብ እና የዋስትና አፈጻጸም አገልግሎት ቀጥተኛ ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት እነርሱ ብቻ ናቸው።"

(111) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.3.3 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

''10.3.3 በምርት ገበያው የሚከናወኑ ግብይቶችን በተሚከተ ማንኛውም አባል በአባሉና በደንበኛው መካከል የተደረሰ የፀና ስምምነት ሣይኖር ውሎችን ሊፈፅም ፣ሊከፍል ወይም ሊዘጋ አይችልም። የስምምነቱ ቅጅ ለምርት ገበያው ማስጠት አለበት። ከዚያ በኋላ ስምምነቱ እስኪያበቃ ድረስ አባሉ በክፍያና ርክብክብ ሚዜፀሚ ካለው ሂሣብ የደንበኛወን ውል ሚዜፀም፣ማዛጋት ወይም ማጥራት አለበት።

(112) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.3.4 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

''10.3.4 ክፍያ ፈጻሚ አገናኝ አባል ተቀባይነት ያለው የክፍያ ሚዜጸሚ አገልግሎት ስምምነት ከሚድረጉ በፊት ክፍያ ሚዜጸም የሚችል ገዢ-ብቻ ወስን ተገበያይ አባልን የመገዣ ገንዘብ የሚስገባት ግዴታ የሚሚከት ክፍያ ለሚዜጸም አይችልም።የስምምነቱ አንድ ቅጂ ለምርት ገበያው ይሰጣል።ከዚህ በኋላ ስምምነቱ እስከቋረጥ ድረስ ክፍያ ሚዜጸም የሚችለው ገዢ-ብቻ ወስን ተገበያይ አባል ለገባቸው ውሎች አገናኝ አባሉ በክፍያና ርክብክብ ሚዜጸሚ  ካለው ሂሳብ ክፍያ ይፈጽሚል።"

(113) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.4.2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

''10.4.2 ተገበያይ አባላት፣ አገናኝ አባላት እና ክፍያ ፈጻሚ ገዢ-ብቻ ተገበያይ አባላት ክፍያ ሚፈጸሚያ ባንክ ሆነው ከተሰየሙ በአንደኛው የባንክ ቅርንጫፍ ወስጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የባንክ ሂሳቦች መክፈት ይኖርባቸዋል።የተጠቀሱት አባላት በምርት ገበያው በሚጠየቀው መሰረት የራሳቸውን እና የደንበኞቻቸውን ገንዘብ፣ የራሳቸውን እና የክፍያ ሚፈጸሚያ ገንዘብ የሚለየትን ጨምሮ የባንክ ሂሳቦችን እንቅስቃሴ በተመለከተ በምርት ገበያው የሚተላለፉ ትእዛዞችን ማክበር ይኖርባቸዋል።ከሚመለከታቸው የባንክ ሂሳቦች የሚፈለገውን ገንዘብ የምርት ገበያው ወጪ በሚደረግ ክፍያዎችን ለመሸፈን እንዲችል የተጠቀሱት አባላት በባንክ ሂሳቦቻቸው ወስጥ በቂ ገንዘብ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል።ሻጭ-ብቻ ወስን ተገበያይ አባላት በክፍያ ሚፈጸሚያ ባንክ ማንኛውም ቅርንጫፍ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ መክፈት አለባቸው። ክፍያ ሚፈጸም የሚችሉ ገዢ-ብቻ ወስን ተገበያይ አባላት የመግዣ ገንዘብ የማስገባት ግዴታቸውን በአገናኝ አባል በኩል የሚወጡ በመሆኑ የክፍያ ሚፈጸሚያ የባንክ ሂሳብ መክፈት አይጠበቅባቸውም።
"

(114) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 10.4.2.3 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.4.2 ስር ተጨምሯል፡፡

"10.4.2.3 ከላይ ከተገለጸው የባንክ ሂሳብ በተጨማሪ፣ ለራሱና ለሌሎች የሚገበያይ አገናኝ አባል በደንበኛው ጥያቄ ሲቀርብለት የደንበኛውን የተለየ ሂሳብ በንዑስ አንቀፅ 4.5.2 መሰረት በመክፈት የጋራ የባንክ ሂሳብ ከተፈተላቸው ደንበኞች ለይቶ ማጠቀም ይችላል;

ሀ. የአባላት ለደንበኛ የመግዣ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሣብ

ለሌሎች የሚገበያዩ አባላት የመግዣ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሣብ መክፈት አለባቸው። ይኸም ደንበኞቻቸው የግዢ ገንዘብ የሚያስተላልፉበት ሂሳብ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ መሆን አለበት ።

I. አባሉ የመግዣ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሣብ ሕጋዊ ባለቤት መሆን፣
II. ለምርት ገበያው ያለ ቅድመ ሁኔታ የወጪ ክፍያ ለማጠየቅ ብቸኛ መብት የሚሰጥ ወክልና ሠነድ በአባሉ ሚፈረም፣
III. የደንቡ አንቀጽ 10.6.4 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አባሉ ከባንክ ሂሣብ ገንዘብ ለማውጣት የሚፈቀድለት መሆን፣
IV. የምርት ገበያው የተጣራ ኤሌክትሮኒክስ ሂሳብ ስሌት ወደ ሂሳቡ ለማስገባት የሚያስችለው ወክልና መኖር፣
V. የምርት ገበያው የኤሌክትሮኒክስ የተከፋይ ወጪ ማጠየቂያ ትዕዛዝ ወደ ሂሣቡ ለመላክ የሚያስችለው ወክልና መስጠት፣
VI. ከሂሣቡ ተከፋይ ሊሆን የሚችል ቼክ መስጠት የሚይቻል ስለመሆኑ እና
VII. ከባንክ ሂሣቡ ተከፋይ የሚሆን የክሬዲትና ደቢት ካርድ ማውጣት አለመቻሉ።

ለ. የአባላት ለደንበኛው የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ

ስለሌሎች የሚገበያዩ አባላት የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ የደንበኛ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ መክፈት አለባቸው።

i. አባሉ የደንበኛ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ ሂሳብ ሕጋዊ ባለቤት መሆን፣
ii. አባሉ ተከፋይ ወጪ ለማጠየቅ ብቸኛ መብት ያለው መሆን፣
iii. ለደንበኞቹ የወጪ ክፍያ ለማጠየቅ መብት የሚሰጥ ወክልና ሠነድ በአባሉ ሚፈረም፣
iv. አባሉ የደንበኛ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሁሳብ ወስጥ ያለን ገንዘብ ወዲያውኑ ለደንበኞች በባንክ ሂሳባቸው ወስጥ በማስገባት ማከፋፈል አለበት፣
v. የምርት ገበያው የኤሌክትሮኒክስ ተከፋይ ገቢ ትዕዛዝ ለመስጠት ወክልና መኖር፣"

(115) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.4.3.1(ለ)(ii) እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

''ii. ለተገበያይ አባላት፣ ለአገናኝ አባላት እና ለክፍያ ፈጻሚ ገዢ-ብቻ ወሰን ተገበያይ አባላት የሚሟከተው ቅርንጫፍ ባንክ ወይም ለወሰን አገናኝ አባላት እና ለሻጭ-ብቻ ወሰን ተገበያይ አባላት ደግሞ በክፍያ ሚጺጸሚ ባንክ ሜቸወም ቅርንጫፍ፣"

(116) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.4.3.4 (ሐ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

''ሐ. የምርት ገበያው ከክፍያ ሚፀሚ ባንኩ አጠቃላይ የመገዣ ገንዘብ ማከገቢያ የባንክ ሂሣብ ገንዘብ ለማውጣት እንደዚሁም የአባላት የሽያጭ ክፍያ ግዴታ ለመወጣት  በክፍያ ሚፀሚ ባንክ ወስጥ ወዳለው የምርት ገበያው የክፍያ ሚጸሚ ባንክ ሂሣብ እንዲዘወር የክፍያ ሚፀሚ ባንኩን ለማጠየቅ ብቸኛ መብት ያለው መሆኑን"

(117) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.4.4 እና10.4.6 እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

''10.4.4 የተሰየመው የክፍያ ሚጸሚ ባንክ ከምርት ገበያው ወይም ከክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ የተሰጠዋ ትእዛዝ ስለሚጸም

የተሰየመው ክፍያ ፈጻሚ ባንክ በምርት ገበያው ወይም በክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ  ሲታዘዝ በምርት ገበያው ወይም በክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ  የባንክ ሂሳብ ወጪ ገቢ ያደርጋል። እንዲሁም ለተወከለበት የአባላት ክፍያ ሂሳብ ተመሳሳይ ድርጊት ይፈፀሚል።

10.4.6 የክፍያ ሚጸሚ ባንኩ አቋምን ስለሚሳወቅበት ሁኔታ
አባላት ያለባቸውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ካላቸው የመገዣ ገንዘብ ማከገቢያ የባንክ ሂሳብ ለመውጣት የገንዘብ እጥረት ካጋጠመ ክፍያ ሚፀሚ ባንኩ ስለሁኔታው ለምርት ገበያው የክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማምርያ ስራ አስኪያጅ በጋራ በተስማማበት የማናኛ መንገድ ማሳወቅ ይኖርበታል።"

(118) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.5.1.1 እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

"10.5.1.1 አባላት ግብይት ከሚካሂዱበት ቀን በፊት ባለው የሚጨረሻ የገበያ ቀን ከቀኑ 9፡30 ድረስ የምርት ገበያ የግዢ ገንዘብን በመገዣ ገንዘብ ማከገቢያ የባንክ ሂሳብ ገቢ ሚድረግ አለባቸው።በተጨሜሪም በከሰዓት በኋላ የግብይት ክፍለ ጊዜ ምርት ለመግዛት ገዥ በግብይቱ ቀን ከጥዋቱ 4፡00 ድረስ የግዢ ገንዘብን በመገዣ ገንዘብ ማከገቢ የባንክ ሂሳብ ገቢ ሚድረግ አለበት። የምርት ገበያው የግዢ ገንዘብን በመገዣ ገንዘብ ባንክ ማከገቢያ ጊዜ በተመለከተ ቦርዱን እና ባለስልጣኑን በተቻለ ፍጥነት በማሳወቅ በየጊዜው ማሻሻል ይችላል፡፡"

(119) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 10.5.1.2 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.5.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዑስ አንቀፅ 10.5.1.2 እስከ ንዑስ አንቀፅ 10.5.1.4 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 10.5.1.3 እስከ 10.5.1.5 በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

"10.5.1.2 አባላት የምርት ገበያ የግዢ ገንዘብን በመገዣ ገንዘብ ማከገቢያ የባንክ ሂሳብ ገቢ ሚድረግ ያለባቸው ከባንክ ሂሳብ በማከተላለፍ ብቻ መሆን አለበት።"

(120) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.5.2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

"10.5.2 የክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ከሁሉም ግብይት የሚመነጩ ክፍያዎችን ሚጸም ያለበት ስለመሆኑ

10.5.2.1 የክፍያና ርክብክብ ሚጸሜ ተዛሜጅ ከሆኑ ግብይቶች የሚመጩ ክፍያዎች ተፈጻሚ ሜድረግ ያለበት ሲሆን በክፍያ አፈፃፀም አባሉ ለክፍያና ርክብክብ ባለበት የተጣራ ዕዳ ማጠን ብቻ የምርት ገበያወን ምትክነት ሜቀበል ይኖርበታል።

10.5.2.2 የግዥ ወይም የሽያጭ ትዕዛዝ ተዛሜጅ ግብይት የሚሆነው በንግድ ሥርዓት ወስጥ የተያያዘ ሲሆንና ሌሎች ግምት ወስጥ ከሚገቡ ጉዳዮች አንፃር የክፍያና ርክብክብ ሚጸሜ ትዕዛዙን ዋጋ አልባ ሆኖ ካላገኘው ነው።

10.5.2.3 የክፍያና ርክብክብ ሚጸሜ ወሉ ተዛሜጅ ሆኖ ካገኘው አባላቱ በማንኛወም ምርት ወል ላይ ላለባቸው የተጣራ የገንዘብ ዕዳ በሙሉ ተቃራኒ ወገን ሆኖ በምትክነት ይገባል።"

(121) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.6.1.1 እና 10.6.1.2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

"10.6.1.1 የክፍያና ርክብክብ ሚፀሜ በአባላት የተፈጸመ ግብይትንና በክፍያና ርክብክብ ሚጸሜ የተዛመደን ግብይት መሠረት በሜድረግ የክፍያ ሚጸሜ ክፍል የአባላትን የተጣራ ግዴታ መግለጫ ማዘጋጀትና ከግብይቱ ቀን ቀጥሎ ባለው የገበያ ቀን ከጥዋቱ 2፡00 ላይ እያንዳንዱ አባል ስለ መግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ እና የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሣቦች አስሜልክቶ ያለበትን ግዴታ ለአባላቱ ማሳወቅ አለበት። በአባላት የተጣራ ግዴታ ላይ የተሰጠው መግለጫ በአባላት ላይ አስገዳጅነት አለው።

10.6.1.2 ተገበያይ አባላት፣አገናኝ አባላት ፣ክፍያ ፈጻሚ ገዢ-ብቻ ወስን ተገበያይ አባላት እና ሻጭ-ብቻ ወስን ተገበያይ አባላት በእያንዳንዱ የግብይት ቀን ማገስት በሚገኝ የግብይት ቀን የክፍያና ርክብክብ ሚጸሜ ማምርያ የሚሰጠዋን የተጣራ የግዴታ መግለጫ የመዉሰድ ግዴታ አለባቸው። የምርት ገበያው የተጣራ የግዴታ መግለጫ ለአባላት በኤሌክትሮኒክስ በሜገዝ ለመላክ ይችላል::"

(122) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.6.2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"10.6.2 ደህረ ንግድ ክፍያ አፈፃፀም

10.6.2.1 ስለ ገንዘብ ዝወውር

የክፍያና ርክብክብ ሚጸሜ ማምርያ ስለ አባላት የመግዢያ ገንዘብ ከአባላት የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ወይም ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ ከአባላት ደንበኛ የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ወይም ከአባላት የክፍያ ሚጸሜ የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ የተጣራ የሽያጭ ክፍያ/ግዴታ ከግብይቱ ቀን ቀጥሎ ባለው የገበያ ቀን ከጥዋቱ 2፡00 እስከ 3፡00 ድረስ በወጪ ተከፋይ ማዛዝ አለበት።"

(123) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.6.3 የመጀመርያ አረፍተ ነገር እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"10.6.3 በክፍያ አፈፃፀም ላይ ስለሚደረጉ ማስተካከያዎች

በአባላት የሚፈፀሙ ተዛሜጅ መሆናቸው በክፍያና ርክብክብ ሚጸሜ የተለዩ ወሎች በክፍያ አፈፃፀም ሂደት አማካኝነት በየእለቱ በአባላቱ ሳይፈፀሙ በቀሩ ወሎች ወይም ሳይከፈሉ በቀሩ ሌሎች ዕዳዎች ክፍያ አፈፃፀም ይገዛሉ/ ሊገዙ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱ የሚስተካከያ የክፍያ አፈፃፀም የሚከተሉትን ልዩነቶች ያጠቃልላል።"

(124) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.6.3(ሠ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"ሠ. በንኡስ አንቀጽ (ሐ) እና (መ) ከተጠቀሱት ወጭ የሆኑ የማዘን አገልግሎት ክፍያዎች (የገዢ ወጪ ተከፋይ)"

(125) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 10.6.3 (በ) በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.6.3 ስር ተጨምሯል፡፡

" (በ) ሌሎች ተፈጻሚ የሚሆኑ ክፍያዎች፡፡ >>

(126) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.6.4.2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"10.6.4.2 የምርት ገበያው የክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ ጥያቄወን በተቀበለ 48 ሰዓታት ወስጥ ገንዘቡን ከአባሉ ወይም ከደንበኛው የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ ወስጥ ለማውጣት እንዲቻል ዝግጁ ሚድረግ አለበት።"

(127) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.6.5 የመጀመሪያ አረፍተ ነገር እና ንዑስ አንቀፅ 10.6.5 (ለ) ፣ (ሐ) እና (መ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"10.6.5 በክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ የተሰበሰቡ የተለያዩ ክፍያዎችን ሪፖርት ስለሚድረግ እና ስለማስተላለፍ፡፡

የምርት ገበያው የክፍያ ሚጸሚ የባንክ ሂሳብ ከክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ የሂሳብ ማዝገብ ጋር በየወሩ ሚጨሻ እንዲታረቅ ሚረግ አለበት፡፡ በዚሁ ሚሰረት የሚከተሉት አይነት ሪፖርቶች እና ዝወወሮች በክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ ሚከናወን አለባቸው፡፡

ለ. የምርት ገበያው የክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ ከምርት ገበያው የክፍያ ሚጸሚ የባንክ ሂሳብ የሰበሰበወን የቅድሚ ገቢ ግብር ወደ ምርት ገበያው ኮርፖሬት የባንክ ሂሳብ በየወሩ ማዛወር አለበት፡፡ ይሁን እንጂ የምርት ገበያው ገንዘብ ፍላጎት ከግምት በማስገባት እና ይሄው በዋና ስራ አስፈፃሚው ሲጸድቅ የፋይናንስ ዋና ማጥያ በወሩ በማንኛውም ጊዜ ወስጥ ይህ ገንዘብ እንዲዛወርለት ማጠየቅ ይችላል፡፡ የክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ ከምርት ገበያው የክፍያ ሚጸሚ የባንክ ሂሳብ የሰበሰበወን እና ለፋይናንስ ዋና ማጥያ ያዘዋወረወን በየወሩ ሪፖርቱ ማስታረቅ አለበት፡፡

ሐ. የክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ ከምርት ገበያው የክፍያ ሚጸሚ የባንክ ሂሳብ የሰበሰበወን የግብይት ክፍያ፣ የመጋዘን ቁጥጥር ክፍያ፣ የመጋዘን አገልግሎት ክፍያ፣ ሌሎች የመጋዘን ክፍያዎች፣ በምርት ገበያው ክፍያዎች ላይ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የእስፖርት መዋጮዎች በሙሉ ወደ ምርት ገበያው ኮርፖሬት የባንክ ሂሳብ በየወሩ ማስገባት አለበት፡፡ ይሁን እንጂ የምርት ገበያው የክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ ከምርት ገበያው የክፍያ ሚጸሚ የባንክ ሂሳብ የሰበሰበወን እነዚህን ክፍዎች በሙሉ የምርት ገበያው ገንዘብ ፍላጎት ከግምት በማስገባት እና ይሄው በዋና ስራ አስፈፃሚው ሲጸድቅ የፋይናንስ ዋና ማጥያ በወሩ በማንኛውም ጊዜ ወስጥ ይሄው ገንዘብ እንዲዛወርለት ማጠየቅ ይችላል፡፡ የክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ ከምርት ገበያው የሰበሰበወን እና ለፋይናንስ ዋና ማጥያ ያዘዋወረወን ይሄው ገንዘብ በየወሩ ሪፖርቱ ማስታረቅ አለበት፡፡

መ. የክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ "ከወጪ ገበያ ምርት ላይ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ" እና አጠቃላይ "የቅድሚ ገቢ ግብር" አግባብነት ያለው ዳታ የኤሌክትሮኒክ ቅጂ ለምርት ገበያው የፋይናንስ ዋና ማሜሪያ በየወሩ ማቅረብ አለበት፡፡ የፋይናንስ ዋና ማሜሪያ የዳታወን ቅጂ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡"

(128) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.6.6 የመጀመሪያ አረፍተ ነገር ንዑስ አንቀፅ 10.6.6.1 በሚኬ ተስተካክሎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"10.6.6 በክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ የሚጸም ደህረ ክፍያ አፈጻጸም ማስተካከያዎች

በአባላት ተፈርመው በክፍያና ርክብክብ ሚጸሚ ማጥያ የተዛመዱ እና ክፍያ የተፈጸመባቸው ወሎች በሚከተሉት ምክንያቶች ደህረ ክፍያ አፈጻጸም ማስተካከያ ይደረግባቸዋል፡፡

i.ከአፈጻጸም ዋስትና ጋር ለተያያዙ አቤቱታዎች/የመብት ጥያቄዎች፣

ii. ከተገቢው ማጠን በላይ በማስለፍ የሚደረግ ርክክብ፣ ወይ

iii. የክፍያ ስህተቶችን ጨምሮ ለሌሎች በክፍያ አፈጻጸም ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች፤

የክፍያና ርክብክብ ሚጸሚያ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች እንዳስፈላጊነቱ የገቢ እና/ወይም ወጪ ተከፋይ ገንዘብ ማስታወሻ በማዘጋጀት የደህረ ክፍያ አፈጻጸም ማስተካከያ ማድረግ አለበት፡፡"

(129) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 10.6.6.2 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.6.6 ስር ተጨምሯል፡፡

"10.6.6.2 የምርት ገበያው የደህረ ክፍያ አፈፃፀም ተግባር በተቀናጀ ሚሌኩ ሚጸማን ለሚያጋገጥ የሚደዳ በየጊዜው የሚሻሻል ስርዓት በመቅረጽ ስራ ላይ ሊያወል ይችላል ፡፡"

(130) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 10.8.1 (ሐ)፣ (መ) ፣ (ሠ) እና (ሰ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"ሐ. ክፍያ ሚጸሚያ ባንኩ ለምርት ገበያው በሰጠው የሚጀ ስህተት ምክንያት ኃላፊ ከሆነ፣የሚፈጠሩ የገንዘብ እጥረቶችን ከግብይቱ ቀን በኋላ ባለው የገበያ ቀን ከጥዋቱ 4፡30 ድረስ ያስተካክላል። በዚህን ጊዜ አባሉ በባንኩ በተፈጠረው ስህተት ተባባሪ እንዳልሆነ የምርት ገበያው የህግ ማስከበሪያ ዋና ማምሪያ ካጣ የአባሉ የግብይት መብቶች እና የመብት መተላለፎች ተፈፃሚነት እንዲቀጥል ይደረጋል፣

መ. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 10.8.1(ሐ) የተመለከተው ተፈፃሚ የሚሆን ከሆነ፣ የክፍያና ርክብክብ ሚጸሚያ ማምርያ አባሉ ግብይቱ ከተካሄደበት ቀን ቀጥሎ ባለው የገበያ ቀን ከጥዋቱ 3፡00 ድረስ በራሱ አግባብነት ያለው የመገዣ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሣብ የጐደለውን ገንዘብ እንዲያስገባ ሊጠይቀው ይችላል። አባሉ ይህን የሚፈፅም ከሆነና የምርት ገበያው የህግ ማስከበሪያ ዋና ማምሪያ ከተፈቀደው ማጠን በላይ በተፈጸመው ግብይት ላይ ተባባሪ አለመሆኑን ከተረዳ የማብየት መብቱና የመብት ማስተላለፍ መብቱ እንደገና ተፈፃሚነት ያገኛል፣

ሠ. ንዑስ አንቀጽ 10.8.1 /መ/ ከተሟላ፣ የክፍያ ርክብክብ ሚጸሚያ ማምርያ የክፍያ ሚጸሚያ ባንኩን ከመገዣ ገንዘብ ማስቀመጫ የባንክ ሂሣብ ከአባሉ የሚፈለገውን ክፍያ ወደ ክፍያና ርክብክብ ሚጸሚያ ማምርያ ሂሣብ እንዲያስተላለፍ ያዘዋል። ያልተከፈለ ቀሪ/ካለ/፣ በንዑስ አንቀጽ 10.8.1 /ረ/ ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ለጉደለቱ የሚካካሻ ክፍያ ይሆናል፣

ሰ. አንድ አባል ክፍያ ባለሚፈፀም ከታገደ የምርት ገበያው የህግ ማስከበሪያ ዋና ማምሪያ ምርመራውን እስከሚያጠናቅቅ ድረስ የአባሉ የግብይት መብት ታግዶ ይቆያል። አባሉ የማጭበርበር ተግባር የፈፀመ አለመሆኑ በህግ ማስከበሪያ ዋና ማምሪያ ከተረጋገጠ በግብይት መብቶቹ ማጠቀሙን የሚቀጥል ሲሆን ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን የግብይት መብቶቹና አባልነቱ ይቋረጣል።"

(131) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 11.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

<<11.1 በማዛን የተቀማጡ ምርቶች ወይም በተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ ያሉ ጭነቶች ርክክብ>>

**(132) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 11.1.2 እና 11.1.5 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡**

<<11.1.2 በምርት ገበያው የሚዘጋጀው የእቃ ማንሻ ማስታወሻ የማንሻወን ቀን፣ ጊዜ፣ የገዢውን ወይም የተወካዩን ስም፣ የስልክ ቁጥር፣ የመታወቂያ ቁጥርና አይነት፣ እና በምርት ገበያው የሚጠየቁ ሌሎች ማናቸውም ሚጃዎችን ማመልከት አለበት። የእቃ ማንሻ ማስታወሻው በምርት ገበያው አባል ወይም በተወካዩ ተፈርሞ ለሚእከላዊ ማከማቻ መቅረብ አለበት። ምርቱ ከማከማቻ ማዛን በሚነሳበት ወቅት ገዢው ወይም ወኪሉ ወቅታዊና አስፈላጊ የሆኑ ሚጃዎችን ይዞ በማከማቻ ማዛኑ ማገኘት አለበት።>>

**(133) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 11.1.5 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡**

‹‹11.1.5 የማስያ ሰነዶችን ትክክለኛነት ካረጋገጠ እና የማንሻ ማስታወሻዎችን ከተቀበለ/ከተረከበ በኋላ የሚከማቹ ማዛኑ ሥራ አስኪያጅ ምርቶቹን ከሚከማቹ ማዛኑ ወይም ከተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራው ለገዢው ወይም ለወኪሉ ያስረክባል። በተጨማሪም የሚከማቹ ማዛኑ ሥራ አስኪያጅ በገዢ ወይም በወኪሉ የቀረበውን የርክክብ ማስታወሻ ቅጂ ትክክለኛነት መመርመር አለበት። ››

**(134) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 11.2.1፣ 11.2.2 እና 11.2.5 እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፡፡**

‹‹11.2.1 ማዛኑ የየዕለቱን የምርት ግብይት ውሎ በተለይም የምርት ግብይቱ ከመጀመሩ በፊት የነበረውን የእያንዳንዱን አባል የምርት አይነትና ማጠን በቀኑ ወስጥ በሚከማቹ ማዛኑ ወይም በተከለለ ጥብቅ ማቆያ ሥፍራው ተቀማጭ እና ወጪ የተደረገውን ምርት፣ እንዲሁም እያንዳንዱ አባል በግብይት ሚዛኛ የሚኖረውን ምርት አይነትና ማጠን (balance) የሚያሳይ ሚዛኛ ለማዛን ኦፕሬሽን ክፍል ማስተላለፍ አለበት።

11.2.2 የማዛኑ ሥራ አስኪያጅ በገዢው ወይም በወኪሉ የቀረበለትን የርክክብ ማስታወሻ ወይም የማንሻ ማስታወሻ ከተቀበለና መርምሮ ካረጋገጠ በኋላ ምርቱን ወይም ጭነቱን ያስረክባል። ስራ አስኪያጁ ምርቱን ካስረከበ በኋላ ገዢውን ወይም ወኪሉን አስፈርሞበት የዕቃዎች ሚከቢያ ማስታወሻ ይሰጠዋል።

11.2.5 ማከማቹ ማዛኑ የዕቃዎች ሚከቢያ ማስታወሻውን ለማዛን ኦፕሬሽን ክፍል በኤሌክትሮኒክስ ማስተላለፍ አለበት። ››

**(135) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 11.2.6 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 11.2 ስር ተጨምሯል፡፡**

‹‹11.2.6 ሽያጭ የተፈጸመባቸው የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካቸው ተለይቶ የታወቀላቸው ምርቶች ከተከለለ ጥብቅ የማቆያ ሥፍራው ክልል ሊወጡ የሚችሉት ገዢው ወይም ህጋዊ ወኪሉ እና ሚዛ የማዛን ተቆጣጣሪው በምርት መሸኛ ደረሰኙ ላይ ከፈረሙበት በኋላ ብቻ ነው፡፡ ››

**(136) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 11.3.8 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 11.3 ስር ተጨምሯል፡፡**

"11.3.8 ገዥው ወይም ወኪሉ ዘግይቶ ለሚከብ እንዲፈቀድለት ለማዕከላዊ ማከማቹ ክፍል የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ምርት ገበያው የማንሻ ማስታወቂያን ስለሚዛዝም ባወጣቸው የአሠራር ሥርዓቶች መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል። ››

(137) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 12.4 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 12 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዑስ አንቀፅ 12.4 እስከ ንዑስ አንቀፅ 12.7 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 12.5 እስከ 12.8 በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

‘’12.4 የምርት ገበያ ዋና ስራ አስፈጻሚ የክፍያና ርክብክብ ሚዲጸምያ ዋስትና ፈንድ ኢንቨስት የሚደረግበትን አሚራጮች አጥንቶ ለወሳኔ የሚያቀርብ ኮሚቴ እንደአስፈላጊነቱ ማሰየም ይችላል፡፡”

(138) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 12.6.1.5 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 12.6 ስር ተጨምሯል፡፡ የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 12.6.1.5 የነበረው ንዑስ አንቀፅ 12.5.1.6 በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

"12.6.1.5 በአባላት ላይ የሚጥሉ የዲሲፕሊን ቅጣት ክፍያዎች ፣የአባልነት ክፍያ እና ደህረ ክፍያ አፈጻጸም ማስተካከያዎች አባሉ እነዚህን ክፍያዎች በደንቡ በተጠቀሰው ጊዜ ወስጥ ካልከፈለ”

(139) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 12.7.1 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"12.7.1 በምርት ገበያው ድንጋጌዎች ሊደነገግ በሚችለው መሠረት አንድ አባል ከግብይት በሚነሣ ጨ በምርት ገበያው የሚፈፀሙ ክፍያዎችንና ርክክቦችን መወጣት ሲያቅተው ወይም አንድ አባል ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑ ሲገለፅ የምርት ገበያው የክፍያና ርክብክብ ማሮያ አስቀድሞ በቦርዱ በሚወድቅ የአባሉን የክፍያ ርክክብ ሚፈፀሚ ዋስትና ፈንድና ሌሎች ገንዘቦች እንዳስፈላጊነቱ ግዴታውን ለማሟላት በሚከተለው ቅደምተከተል መሠረት ማጠቀም ይቻላል፡ –

12.7.1.4 በምርት ገበያው ወይም በክፍያና ርክብክብ ማሮያ ለሰጥ በሚችለው መሠረት የክፍያና ርክክብ ሚፈፀሚ ዋስትና ፈንዱን ኢንቨስት በሚደረግ ወይም በሚሸጥ የሚገኙ ወይም የቅጣት ክፍያዎች፣ ወለድ ወይም ሌላ ገቢ ካለ፣"

(140) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 12.8.2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"12.8.2 በምርት ገበያው ድንጋጌዎች በተደነገገው መሠረት መዋጮ ወይም ተቀማጭ እንዲያደረግ የሚጠቅበት አባል ይህን ሳይፈፅም ቢቀር፣ የዳይሬክተሮች ቦርዱ በየጊዜው በሚወስነው መሠረት ሊከፈል በሚገባው ገንዘብ ላይ ወለድ መጣል እና የገንዘብ ቅጣትን ጨምሮ ተገቢውን የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወስድ ይችላል። አባሉ ከላይ በተጠቀሰት ድንጋጌዎች መሠረት በዳይሬክተሮች ቦርድ የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደበት መሆኑ ወይም አባሉ በማንኛውም ምክንያት የምርት ገበያው አባልነቱ መቅረቱ ለክፍያና ርክብክብ ሚፈፀሚ ማሮያ ወይም ለምርት ገበያው አባሉ ያለበትን ግዴታ ወይም በምርት ገበያው ደንቦችና ተፈፃሚ በሚሆኑ ህግጋት መሠረት አባሉ ለክፍያና ርክብክብ ሚፈፀሚ ማሮያ ወይም ለምርት ገበያው የሚኖርበትን ማንኛውም ግዴታ አያስቀረውም።"

(141) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 15.1.3 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"15.1.3 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው የሚከተሉትን ስድስት አባላት ማካተት አለበት፡፡"

(142) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 15.1.3.3 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"15.1.3.3 በምርት ገበያው አባላት ማህበር የሚሚጡ በሚልካም ስማቸው የሚታወቁ እና ላለፉት ሁለት አመታት የዲሲፕሊን እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሶስት የምርት ገበያው አባላት፡፡"

(143) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 15.1.5 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"15.1.5 የምርት ገበያው የሕግ ማከበሪያ ዋና መሜሪያ የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው ድምጽ የማስጠት መብት የሌለው ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡"

(144) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 15.2.3.3 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 15.2.3 ስር ተጨምሯል፡፡

"15.2.3.3 በምርት ገበያው የተቀማጡ ኤሌክትሮኒክስ ግብይት መድረክ ስነ ስርዓት ደንቦችን አለማክበር"

(145) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 15.3.1 የመጀመሪያ አረፍተ ነገር እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"15.3.1 አንደኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋት የፈጸመ አባል እንደሚከተለው ይቀጣል፡፡"

(146) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 15.3.2 የመጀመሪያ አረፍተ ነገር፣ ንዑስ አንቀፅ 15.3.2.1 እና ንዑስ አንቀፅ 15.3.2.3 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

" 15.3.2 ሁለተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋት የፈጸመ አባል እንደሚከተለው ሊቀጣ ይችላል፡፡

15.3.2.1 በቦርድ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.2 በተቀመጠው ማስረት ከምርት ገበያው አባልነት ይታገዳል እና/ወይም

15.3.2.3 በቦርድ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በምርት ገበያው የወሳኔ ሃሳብ ማስረት የምርት ገበያው አባልነት ይቋረጣል፡፡"

(147) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 15.4 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"15.4 ስለ ምርመራ እና የዲሲፕሊን ጉዳዮችን ስለመወሰን

15.4.1 ስለ ምርመራ

15.4.1.1 የዲሲፕሊን ጥፋቶችን ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው በደንቡ የተቀመጠው የአባላት ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ጉዳት ደርሶብኛል የሚልን ጨምሮ ማንኛውም ሰው የደንቡን መጣስ በተማለከተ የቃል ወይም የጽሁፍ አቤቱታ ለሕግ ማከከበሪያ ዋና ማምሪያ ለማቅረብ ይችላል፡፡ የሕግ ማከከበሪያ ዋና ማምሪያ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በዋና ስራ አስፈጻሚ ወይም በቦርድ ጥያቄ ምርመራ ሊጀምር ይችላል፡፡

15.4.1.2 የሕግ ማከከበሪያ ዋና ማምሪያ የዲሲፕሊን ጥፋትን የሚማለከት ክስ፣አቤቱታ፣ ጥቆማ ወይም ሪፖርት እንደደረሰው ቅድመ ምርመራ ማጣሪያዎችን በማድረግ ሙሉ ምርመራ ስለማከፈለጉ መወሰን አለበት፡፡

15.4.1.3 ሙሉ ምርመራ ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሕግ ማከከበሪያ ዋና ማምሪያ ከምርት ገበያው ግብይት ጋር የሚገናኙ ማስቸወንም ሚጃ የምርት ገበያው ደንብ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ማስቸወም ሰው በማጠየቅ ምርመራ ማከናወን አለበት፡፡ ማስቸወም አግባብነት ያለው ሰው ቀርቦ ቃሉን እንዲሰጥ የሕግ ማከከበሪያ ዋና ማምሪያ ሊጠራው ይችላል፡፡

15.4.1.4 በሕግ ማከከበሪያ ዋና ማምሪያ ተጠርቶ የቀረበ ሰው የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ማስቸወም ጥቅም እንደሚያገኝ የተስፋ ቃል ሊሰጠው አይገባም፡

15.4.1.5 ከአራተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ውጭ የሆነ ደንብ መጣስ ተፈጽሟል ብሎ የሕግ ማከከበሪያ ዋና ማምሪያ ካመነ የምርመራ ሪፖርት እና ክስ ለግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ማቅረብ አለበት፡፡

15.4.1.6 የሕግ ማከከበሪያ ዋና ማምሪያ ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበው ክስ በበቂ ማስረጃ አልተደገፈም ብሎ ከወሰነ ጉዳዩን በመዝጋት ለአቤቱታ አቅራቢው እና ለዋና ስራ አስፈጻሚ ያሳውቃል፡፡

15.4.1.7 የሕግ ማከከበሪያ ዋና ማምሪያ ጉዳዩን በመዝጋቱ ቅሬታ ያደረበት ሰው ወሳኔው በተሰጠ አስር የስራ ቀናት ወስጥ ይግባኙን ለግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ለማቅረብ ይችላል፡፡"

(148) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 15.4.2.3 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 15.4.2 ስር ተጨምሯል፡፡

"15.4.2.3 በምርት ገበያ ዋና ስራ አስፈጻሚ ሲጸድቅ የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ እንደጥፋቱ ክብደት እና አይነት ጉዳዩ ተጣርቶ ወሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የመድረክ ተወካይ ወይም አባል ከምርት ገበያ መድረክ ለአንድ ወር ጊዜ አግዶ ማቆየት ይችላል፡፡"

(149) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 15.4.3 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 15.4 ስር ተጨምሯል፡፡ከንዑስ አንቀፅ 15.4.3 እስከ ንዑስ አንቀፅ 15.4.5 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 15.4.4 እስከ 15.4.6 በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

"15.4.3 የቀደሞ ቅጣት ሪከርድ እና የይርጋ ጊዜ

15.4.3.1 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ቅጣት በሚወሰንበት ጊዜ የጥፋተኛውን የቀደሞ የዲሲፕሊን ቅጣት ሪከርድ ከግምት ወስጥ ማስገባት አለበት::

15.4.3.2 የጥፋተኛው የቀደሞ የዲሲፕሊን ቅጣት ሪከርድ ቅጣቱ ከተጣለበት ከአንድ አመት በኋላ እንደ ጥፋት ሪከርድ ሊቆጠር አይችልም::"

(150) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 15.4.5.1 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"15.4.5.1 የሕግ ማስከበሪያ ዋና ማሞሪያ የምርት ገበያውን የዲሲፕሊን ወሳኔ አፈጻጸም መከታተል አለበት፡፡"

(151) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 16.2.2.8.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

<<16.2.2.8.2 ገዥው በናውን ተረክቦ በናው መኪና ላይ ከተጫነ በኋላ መኪናው የምርት ገበያውን ማዛን ግቢ ከሚለቀቁ በፊት ገዥው ወይም ተወካዩ እና የግብርና ሚኒስቴር የቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል ሰራተኛ በተገኙበት ከእያንዳንዱ መደብ አጠቃላይና ወካይ የሆነ አንድ ኪ.ግ. የሚሆን ቡና ከያንዳንዱ ከረጢት ላይ የምርት ገበያው ናሙና መውሰድ አለበት:: ናሙናው በሶስት ተከፍሎ አንዱ በምርት ገበያው የሥራ ናሙና፣ ሁለተኛው ክፍል በምርት ገበያው ደህንነቱ በተጠበቀ እቃ በጥንቃቄ የሚቀመጥ ሆኖ በምርት ገበያውና በግብርና ሚኒስቴር የቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል የተመደበ ሰራተኛ በጋራ የሚይዙት ዋቤ ናሙና ሲሆን ሶስተኛው ለገዥው ወይም ለወኪሉ የሚሰጥ የጭነት ናሙና ይሆናል::>>

(152) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 19(1) (ኀ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"ኀ. የምርት ግብይት ደንቦች ወይም የከፋያና ርክብክብ ደንቦች ድንጋጌዎችን ማሻሻል ወይም ማገድ።"

3. **ስለደንቡ ተፈጻሚነት**

ይህ የተሻሻለ ደንብ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር 551/2000 አንቀጽ 6(3) መሰረት በባለሥልጣኑ እንደጸደቀ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

**በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ቦርድ ሰኔ 15 ቀን 2009 ዓ.ም በአዲስ አበባ ጸደቀ፡፡**